እፕድ

# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 290 ሰኔ 20 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

## በመጪዎቹ ሰባት ዓመታት

### ለሁሉም ኢትዮጵያውያን በአቅራቢያቸው ንጹህ የመጠጥ ውሃን ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ ነው

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- እ.ኤ.አ በ2030 ለሁሉም ዜጎች በአቅራቢያቸው ንጹህ የመጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ። የውሃ ሀብት አስተዳደር እና የኢነርጂ የባለብዙ ባለድርሻ አካላት ፎረም ተካሂዷል።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር 11ኛው የባለድርሻ አካላት የጋራ ጉባኤ "የተፋጠነ ትግበራና የተሻሻሉ ተጽእኖ ተከታታይነት ላለው እድገትና ለውጥ" በሚል መሪ ቃል የውሃ ሀብት አስተዳደር እና የኢነርጂ የባለብዙ ባለድርሻ አካላት ፎረም ትናንት ተካሂዷል።

በፎረሙ ላይ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ እንደገለጹት፤ የባለድርሻ አካላት ፎረም ዋና ዓላማ በመጠጥ ውሃ፣ በኢነርጂ፣ በአካባቢ ጥበቃና በሳኒቴሽን ዘርፍ እስካሁን ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጋር በጋራ የሚሰሩ ተቋማትና ድጋፍ የሚያደርጉ የልማት ድርጅቶች ኢትዮጵያ ምን ላይ ደርሳለች በሚለው ጉዳይ ላይ የጋራ መግባባት መፍጠር ነው።

ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋምና ለመከላከል የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርና የአረንጓዴ ኢነርጂ የማልማት ስራ ፋይዳው ምን እንደሚመስል ማቅረብ አስፈላጊ እንደሆነም ጠቁመዋል።

ኢንጂነር ሀብታሙ፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባለፉት ዓመታት በመጠጥ ውሃ ማዳረስ፣ በሳኒቴሽን፣ በሀይጅንና በኢነርጀው ዘርፍም ታዳሽ ኃይል በመጠቀም ዜጎቻችን ከብክለት ነጻ የሆነ ኢነርጂ ማቅረብ ለማስቻል ታቅዶ ሲሰራበት ቆይቷል ብለዋል።

የመጠጥ ውሃ አሁን ካለበት ዝቅተኛ ሽፋን እ.ኤ.አ በ2030 ለሁሉም ዜጎች በሚባል ደረጃ በአቅራቢያቸው ንጹህ ውሃ ማግኘት እንዲችሉ

በመጪው ሰባት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ



## ብሩህ ኢትዮጵያ ውድድር

### ችግሮችን ወደ ዕድል መቀየር እንደሚቻል የታየበት ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ብሩህ ኢትዮጵያ 2015 ብሔራዊ የሥራ ፈጠራ ሃሳብ ውድድር እንደ ሀገር ያሉ ችግሮችን ወደ ዕድል መቀየር እንደሚቻል የታየበት መሆኑን የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል ገለጹ፡፡ የብሩህ ኢትዮጵያ 2015 ብሔራዊ ውድድር የማጠቃለያ ሽልማት ሥነሥርዓት ትናንት ተካሂዷል፡፡

ሚኒስትሯ በብሩህ ኢትዮጵያ 2015 ብሔራዊ ውድድር የሽልማት ሥነሥርዓት ላይ ትናንት እንደገለጹት፤ የፈጠራ ሃሳቦች ከችግር አልያም በየአካባቢው ያሉ መልካም እድሎችን በአግባቡ ከመረዳት የሚገኙ ናቸው፡፡ ብሩህ ኢትዮጵያ 2015 ብሔራዊ የሥራ ፈጠራ ሃሳብ ውድድርም እንደ ሀገር ያሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ወደ እድል መቀየር እንደሚቻል የታየበት ነው ብለዋል፡፡

የቀረቡ የሥራ ፈጠራ ሃሳቦች እንደ ትልልቅ

ብሩህ ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## “ሕዝበ ሙስሊሙ የአረፋ በዓልን ሲያከብር የእዝነትንና የመረዳዳትን መንፈስ በማዳበር ሊሆን ይገባል”

\- ኡስታዝ አቡበክር አሕመድ



**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ሕዝበ ሙስሊሙ የኢደል አደሃ (አረፋ) በዓልን ሲያከብር የእዝነትንና የመረዳዳትን መንፈስ በማዳበር ሊሆን ይገባል ሲሉ የሃይማኖት መምህሩ ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ ገለጹ፡፡

ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በበዓሉ ዕለት ሌላው ወንድም አዝኖና ልቡ ተሰብሮ እየኖረ ሌላው ቤት ሞልቶና ደምቆ መታየት የእምነትና

“ሕዝበ ሙስሊሙ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል













## በክልሉ የመማሪያ ክፍሎች ከተማሪዎች ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ አለመሆን ፈታኝ ሆኗል

\- ተማሪዎች በዛፍ ጥላ ሥርና በተጨናነቀ የመማሪያ ክፍል ውስጥ እየተማሩ ነው

ገጽ 6





አቶ አሻግሬ ጀንበሬ

# በክልሉ
## የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት ምርታማነትን በማሳደግ ላይ በትኩረት እየተሰራ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በሲዳማ ክልል የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት የምርት ፍላጎትንና አቅርቦትን ለማመጣጠን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ላይ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን የክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የሲዳማ ክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ አቶ አሻግሬ ጀንበሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በክልሉ ያለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት ፍላጎትና አቅርቦትን ያማከለ የምርት አቅርቦት ሥራ ላይ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል፡፡

ክልሉ በሀገር አቀፍም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተውን የዋጋ ግሽበት መሰረት በማድረግ እንደሀገር የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት የተቀመጡትን ግቦች ተግባራዊ እያደረጉ መሆኑን አቶ አሻግሬ ገልጸው፤ በህብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት የግብርናና የሸቀጣሸቀጥ ምርቶችን አምራቹ ለሸማቹ እያቀረበ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

እንደ አቶ አሻግሬ ገለጻ፤ በዋናነት የዋጋ ንረት ማረጋጋት የሚቻለው ምርታማነትን በመጨመርና በዘርፉ የሚስተዋሉ ሕገ-ወጥ ተግባራትን በመቆጣጠር ነው፡፡ ከዚህ አኳያም በክልሉ ምርታማትን ለማሳደግና ሕገወጥ ተግባራትን በመቆጣጠር ረገድም ከክልል ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ ነው ያሉት፡፡

አቶ አሻግሬ እንዳሉት፤ ምርት በሚሰውሩና በሸማቹ ላይ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ በሚያደርጉ አካላት ላይ ክልሉ በህብረተሰቡ ተሳትፎ ሕገወጦችን በመለየት ርምጃ እየወሰደ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

እንዲሁም የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋትና የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስ የቅዳሜና እሁድ ገበያ ላይ በትኩረት እየተሰራ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ከክልሉ ውጪ የሚገቡ ምርቶች በሚፈለገው ልክ እንዲሁም በወቅቱ እንዲገቡ ከሚመለከተው ባለ ድርሻ አካል ጋር በትብብር እየሰራን ነው ብለዋል፡፡

የዘይትና የስኳር ምርቶች በመንግሥት አመቻችነት የሚገባው ምርት ቆሞ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ የስኳር እና የዘይት ምርቶች ምንም እንኳን የሚፈለገው ያክል ባይገቡም ወሩን ጠብቆ ወደ ክልሉ እየገቡ ነው፡፡ እነዚህ ምርቶችም በሸማቾች ማህበራት በኩል ህብረተሰቡ በተመጣጠኝ ዋጋ እንዲያገኝ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ አሻግሬ ገለጻ፤ የህብረት ሥራ ማህበራት ከአምራቹ ወስደው ለሸማቹ የሚያደርሱበት መንገድ የደላላን ሰንሰለት በማሳጠር ገበያውን ማረጋጋት የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

እንደሀገር የተከሰተው የዋጋ ንረት ወደ ክልሉ በሚገቡ ምርቶች ላይ ተጽዕኖ ፈጥሯል ያሉት አቶ አሻግሬ፤ የምርት አማራጮችን የማግኘት ጉዳይም ሌላኛው ተግዳሮት እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ምርቶች ከመነሻቸው ያለደረሰኝ መገዛታቸው ነጋዴው በፈለገው መንገድ የሚሸጥበት ሁኔታ ፈጥሮለታል ያሉት አቶ አሻግሬ፣ ወቅቱንና የሸማቹን አቅም ባላገናዘበ መልኩ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ ማድረግ እንዲሁም ምርትን በመጋዘን ደብቀው ማስቀመጥ በክልሉ የዋጋ ንረትን ከሚያባብሱ ዐቢይ ጉዳዮች መካከል ናቸው፡፡ ነጋዴው ከዚህ መሰል ሕገ ወጥ ድርጊት እንዲቆጠብና በኃላፊነት ስሜት ህዝቡን በቅንነትና በታማኝነት እንዲያገለግልም አሳስበዋል፡፡

# የግንባታ ቦታዎችን ከሥራ ላይ አደጋና ከጤንነት ስጋት ነጻ ለማድረግ እየተሰራ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዳማ፡- የግንባታ ቦታዎች ከሥራ ላይ አደጋና ጤንነት ስጋት ነፃ ሊሆኑ እንደሚገባ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር አሳሰበ።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ከትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ያዘጋጁት የግንባታ ቦታ ደህንነት እና ጤና ደንብ፣ የሕግ ማዕቀፍና የትግበራ መመሪያ ዝግጅት አውደ ጥናት በትናንትናው ዕለት ተካሂዷል።

በመርሃ ግብሩ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ኢንጂነር ወንድሙ ሴታ እንደገለጹት፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለሀገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ቢኖረውም የኢንዱስትሪው የሥራ ላይ ደህንነት፣ ጤና እና የአካባቢ ደህንነት ሁኔታ የአሁኑን ዘመን የሚመጥን አይደለም።

በዚህም በሰው ሕይወትና አካል ላይ የሚደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው ያሉት ኢንጂነር ወንድሙ፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የግንባታ ቦታዎች ከሥራ ላይ አደጋና ጤንነት ስጋት ነፃ ሊሆኑ ይገባል ብለዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ይህን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በ10 ዓመት መሪ ዕቅድ ውስጥ አካቶ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ ገልጸውም፤ በዚህም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተለያዩ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ከተለያዩ ተቋማት ጋር እያከናወነ ነው ብለዋል።

እንደ ኢንጂነር ወንድሙ ገለፃ፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ላይ የተሳለጠ የአሰራር ሥርዓት እንዲሰፍን፤ የኮንስትራክሽን ሠራተኞች የሥራ ላይ ደህንነት፣ ጤናና አካባቢን ያማከለ የቁጥጥር የሕግ ማዕቀፎችን እንዲሁም ኢንዱስትሪውን በውጤታማነት ለመምራት እና ለማስተዳደር የሚያስችሉ ሥራዎችን እየሰራ ይገኛል። በዚህም በግንባታ ሥራ ላይ የሚፈጠር አደጋን ለመቀነስ የሚያስችሉ ሥራዎች ትኩረት ተደርጎባቸዋል።



ኢንጂነር ወንድሙ ሴታ

ስለዚህ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ፕሮጀክታቸውን በሚቀርፁበት ወቅት የግንባታ ቦታ ደህንነት እና ጤና ደንብ፣ የሕግ ማዕቀፍ እና የትግበራ መመሪያ መዘርጋት ይኖርባቸዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ይህንን ተግባራዊ ላደረጉ ተቋማት ልዩ ድጋፍ እንደሚደረግ ተናግረዋል።

ሠራተኞችም ተገቢውን ሥልጠና በመውሰድ ራሳቸውን ከአደጋ ሊጠብቁ ይገባል። በዚህ ሂደት ባለድርሻ አካላት የራሳቸውን ሚና በመወጣት በሥራ ቦታና በአካባቢ ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን በመቀነስ የዘርፉን በጎ ሚና ማስቀጠል ይገባል ብለዋል።

# በሦስት ክልሎች 54 ሺህ ሄክታር የመኸር ሰብል በተምች ተጠቅቷል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮው የመኸር ሰብል ላይ በሦስት ክልሎች ተምች ተከስቶ 54 ሺህ ሄክታር መሬት መጠቃቱንና 27 ሺህ ሄክታር ሰብል ከጥቃት መከላከል መቻሉን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የዕፅዋት ጥበቃ መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ በላይነህ ንጉሤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሦስት ክልሎች ሰብልን የሚያጠቃ ተምች ተከስቷል። የሰብል ተምቹ በደቡብ ክልል ተከስቶ ወደ አማራና ትግራይ ክልል በመዛመት በአማራ ll፣ በትግራይ ዘጠኝና በደቡብ ክልል ሦስት ወረዳዎች አጥቅቷል።

የሰብል ተምቹ በአማራና በትግራይ ክልል በስፋት እየተዛመተ ነው ያሉት አቶ በላይነህ፤ የተምቹን የመዛመት መጠን ለመቀነስና ለመከላከል ለክልሎቹ የኬሚካል ስርጭት እየተደረገላቸውና የሠለጠነ ባለሙያም እየተላከላቸው መሆኑን አብራርተዋል።

የመኸር ሰብሉ ላይ የተከሰተው ተምች 54 ሺህ ሄክታር መሬት ሰብል አጥቅቷል ብለውም፤ 20 ሺህ ሄክታር መሬት በኬሚካልና ሰባት ሺህ ሄክታሩን በባህላዊ መንገድ ከጥቃቱ መከላከል መቻሉን አስረድተዋል።

እንደ አቶ በላይነህ ገለፃ፤ የሰብል ተምች የሚያራባው የእሳት እራት በሌሊት የሚበርና በአንድ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ መሬት የሚያጠቃ በመሆኑ በተከሰተበት ተቆጣጥሮ ማስቀረት አልተቻለም። በዚህም ምክንያት ተምቹ ወደ ሌሎች ክልሎች በፍጥነት የመዛመት ዕድል አግኝቷል።

በተጨማሪም ተምቹ እንዳይስፋፋ ለማድረግ የኬሚካል ርጭት እንደ አማራጭ መጠቀም ቢቻልም ያለው የኬሚካል ክምችት ለዚህ አመቺ አይደለም ብለዋል። ለአብነትም ተምች የተከሰተባቸውን የሣር ሜዳዎች ኬሚካል በመርጨት ወደ ሰብል እንዳይሰራጭና ከፍተኛ ጉዳት እንዳያደርስ ማድረግ ይቻል እንደነበር ጠቅሰው ነገር ግን ይህን ማድረግ



ከፍተኛ የሆነ የኬሚካል አቅርቦት የሚጠይቅ በመሆኑ ማድረግ አልተቻለም ብለዋል።

ሆኖም ተምቹ ወደ ሌሎች ክልሎች ከመዛመቱ በፊት ለማጥፋት በተለይ በአዋሳኝ አካባቢዎች ኬሚካል መርጨትና ባህላዊ የመከላከል ሥራ መሰራቱን አብራርተዋል።

የሰብል ተምቹ ወደ ኦሮሚያ ክልል እና አፋር ክልሎች ይዛመታል የሚል ስጋት እንዳለ ጠቁመው፤ በነዚህ ክልሎች ተምቹ በሰብል ላይ ጉዳት ከማድረሱ በፊት ለመቆጣጠር የኬሚካል ስርጭት እየተደረገ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ማኅበረሰቡ በሰብል ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ፀረ ሰብል ተባዮች በሚከሰቱበት ጊዜ የግብርና ባለሙያዎችን በማማከርና ምክራቸውን ተግባራዊ በማድረግ በቀላሉ የመቆጣጠር ሥራ መስራት ይኖርበታል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።



# ሁለት ተቋማት የሰሩትን የስንዴ መውቂያ ማሽን ለአብዢ አምራች ኢንዱስትሪዎች አቀረቡ

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በጋራ የሰሩትን የስንዴ መውቂያ ማሽን ለአብዥ አምራች ኢንዱስትሪዎች አቀረቡ፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሀገር ውስጥ እውቀትና ጥሬ እቃን በመጠቀም በጋራ የሰሩትን የስንዴ መውቂያ ማሽን በትናንትናው ዕለት ለተለያዩ አብዥ አምራች ኢንዱስትሪዎች አሸጋግረዋል፡፡

በሽግግር መርሃ ግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቡልልታ፤ የስንዴ መውቂያ ማሽኑ በሀገር ውስጥ እውቀትና ጥሬ እቃ ተሰርቶ ለአርሶ አደሮች ተደራሽ እንዲሆን ሲሠራ ቆይቷል፡፡ በዚህም መሰረት ለአብዥ ኢንዱስትሪዎች ሽግግር መደረጉና ተደራሽ እንዲሆን አስቻይ ሁኔታ መፈጠሩ ለሀገሪቱ አርሶ አደሮች ጊዜና ጉልበታቸውን እንዲቆጥቡ ያደርጋል ብለዋል፡፡

ማሽኑ የአርሶ አደሮችን የሥራ ጫና በመቀነስ ምርትና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የሚረዳ ትልቅ የፈጠራ ሥራ ነው ሲሉም ተናግረዋል፡፡

የሀገሪቱ የስንዴ ምርት እየጨመረ ሲመጣ ቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራ እያደገ መምጣት አለበት ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ቴክኖሎጂን በማስፋፋት የሀገር ውስጥ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት እየተሰራ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የመውቂያ ማሽኑ ለአብዥ አምራች ኢንዱስትሪዎች ሽግግር ተደርጎ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ እንዲሆን መሰራቱ ለአርሶ አደሮች ትልቅ ጥቅም ከመስጠት ባለፈ የውጭ ምንዛሬን በማስቀረት ሀገሪቱ እየገጠማት ያለውን የምንዛሬ እጥረት ይቀርፋል ሲሉ አብራርተዋል።

ማሽኑ ተባዝቶ ለአርሶ አደሮች ተደራሽ እንዲሆን ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ጠቅሰው፣ አብዥ አምራች ኢንዱስትሪዎችም አባዝተው ተደራሽ ለማድረግ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ይወጡ ዘንድ ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ሶፊያ ካሳ በበኩላቸው፤ ቴክኖሎጂን ማምረት ብቻ ሳይሆን ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግ ጠንካራ ሥራ መሰራት አለበት ብለዋል፡፡

በሀገሪቱ የሚሰሩ የተለያዩ ማሽኖች ተመርተው ለተጠቃሚው በተገቢው መንገድ በመዳረስ ጥቅም ላይ ሲውሉ አይስተዋሉም ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ይህ የስንዴ መውቂያ ማሽን በአምራች ኢንዱስትሪዎች ተባዝቶ ለአርሶ አደሮች ተደራሽ እንዲሆን በትኩረት እንሰራለን ሲሉ ቃል ገብተዋል፡፡

ቴክኖሎጂዎችን በማሻሻልና በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ በማድረግ የውጭ ምንዛሬን እጥረት ከመቅረፍ በተጨማሪ የአርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነት ይበልጥ እንዲያድግ የማድረግ ሥራ እየተሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

የስንዴን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ አቅም ለሌላቸው አርሶ አደሮች ማሽኑን ገዝተው እንዲጠቀሙ የብድር አገልግሎት ይመቻችላቸዋል ያሉት ዶክተር ሶፊያ፤ መንግሥት የስንዴ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ በመሆኑ ማሽኑን ለአርሶ አደሮች ተደራሽ በማድረግ አምራች ኢንዱስትሪዎች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

አምራች ኢንዱስትሪዎች ችግር ፈቺ ጥናት በመስራት የግብርና ዘርፉን እያሳደጉ ነው ሲሉ የተናገሩት ደግሞ የማኑፋክቸሪግ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳሬክተር ዶክተር ሚልኬሳ ጃገማ ናቸው፡፡

አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍና ወደ ላቀ ደረጃ በማድረስ የግብርና ዘርፉን የማሳደግና የሀገር ውስጥ ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ እየተሰራ ነው ሲሉም አብራርተዋል፡፡

# በተፋሰሶቹ በ300 ሚሊዮን ዶላር የጎርፍ መከላከልና ተያያዥ ሥራዎች ሊከናወኑ ነው

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- የአዋሽ፣ ዓባይና ሥምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች በሚያካልሏቸው በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች በጎርፍ ሳቢያ የሚደርሱ አደጋዎችን ለመከላከል ከዓለም ባንክ ጋር የተደረሰው የ300 ሚሊዮን ዶላር ሥምምነት ወደ ትግበራ እየገባ መሆኑ ተገለጸ፡፡

በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የአዋሽ ቤዚን አስተዳደር ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አብነት ጌታቸው በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአዋሽ ተፋሰስ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም በዚያው ልክ ከፍተኛ ጎርፍ እና ድርቅም የሚስተዋልበት ተፋሰስ ነው፡፡ ሚኒስቴር መስሪያቤቱ የቅድመ ጎርፍ ማስጠንቀቂያ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከክልሎች ጋር በተናበበ መልኩ ዘርፈ ብዙ ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው፡፡ ይሁንና ከተፋሰሱ በሚገኘው ጥቅም ላይ የሚደረገውን መረባረብ ያክል፤ በጎርፍ ለሚደርሰው አደጋ የመከላከል ሂደቱም ትኩረት የሚፈልግ ነው፡፡

ጎርፍን መከላከል የሁሉንም አካላት ትብብር የሚጠይቅ ነው ያሉት አቶ አብነት፤ «በዚህም ላይ በአፅንኦት እየሰራን ነው፤ በመደበኛ ሥራም የምንሠራቸው ሥራዎች እንዳሉ ሆነው ሌሎች አካላትን በማሳተፍም በጎርፍ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ በትጋት እየሰራን ነው ብለዋል፡፡»

ጎርፍን ለመከላከል ከፍተኛ መዕዋለ ነዋይ የሚጠይቅ መሆኑን የተናገሩት ኃላፊው፤ በአዋሽ የላይኛው ተፋሰስ ክፍል መሠራት ያለባቸው ሥራዎች በሰፊው እየተከናወኑ ነው፡፡ በመካከለኛው እና በታችኛው የተፋሰሱ ክፍልም በጎርፍ የሚደርሰውን አደጋ በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ልዩ ትኩረት በመስጠት እየሰራ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በዚህ ዓመት ችግሮችን ለመለየት ጥረት አድርገናል ያሉት አቶ አብነት፤ መከናወን ያለባቸውን ተግባራት በጥናት ለይተን ወደ ሥራ ገብተናል፤ የተሰጠንን ተልዕኮም እየተወጣን ነው፡፡ በዚህ በጀት ዓመት ከክልሎች ጋር ለመሥራትም ከፍተኛ ጥረት አድርገናል ብለዋል፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርም ባደረገው የዳሰሳ ጥናት መከናወን ያለባቸውን ተግባራት ለይቷል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ከታሰበው ውስጥ አንዱ የጎርፍ አደጋ የሚያስከትለውን የደለል እና መሰል ችግሮችን ለማስወገድ ማሽኖችን በጨረታ በማወዳደር ለሥራ ዝግጁ ማድረግ ሲሆን፤ በመካከለኛው አዋሽ ተፋሰስ ላይ በጨረታው አሸናፊ ተገኝቷል፡፡ ሆኖም የላይኛው እና የታችኛው የአዋሽ ተፋሰስ አካባቢዎች ይህን ማሳካት አለመቻሉን ነው የጽህፈት ቤት ኃላፊው የገለጹት፡፡



አቶ አብነት ጌታቸው

እንደ አቶ አብነት ገለፃ፤ መንግሥት ከአዋሽ ተፋስ በዘለለ በዓባይ እና ሥምጥ ሸለቆ ተፋሰሶችም ጎርፍን ለመከላከል የሚያስችሉ የረጅም ጊዜ ውጥኖችን መጀመሩን አመልክተዋል፡፡ በዚህም ረገድ በቀጣይ አምስት ዓመታት የሚተገበር ጎርፍን የመከላከል ሥራዎች ከወዲሁ መጀመራቸውን አስገንዝበዋል፡፡ ለትግበራው ይረዳ ዘንድም የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ከዓለም ባንክ ጋር የ300 ሚሊዮን ዶላር ሥምምነት መፈፀሙን አመልክተዋል፡፡ ትግበራውም ከሐምሌ ወር የሚጀምር ሲሆን በቀጣይ በአገር ደረጃ በጎርፍ የሚደርሱ አደጋዎችን በከፍተኛ ደረጃ የሚያቃልል መሆኑን አቶ አብነት አረጋግጠዋል፡፡

# ስለጤናም ስለጤናው ዘርፍም የቀረበው አውደርዕይ


**ራስወርቅ ሙሉጌታ**



ወይዘሪት ተምኪን አክበር



አቶ መላኩ አበራ፤



ዶክተር ሮቤል ስንታየሁ



ሲስተር ይርጋአለም ከበደ

የተንጣለለው የአዲስ አባባ ሳይንስ ሙዚየም ዛሬም በበርካታ ሰዎች እየተጎበኘ ይገኛል። ሙዚየሙ በጤና ሚኒስቴር አዘጋጅነት በአዲስ አበባ ሳይንስ ሙዚየም እየተካሄደ ያለውና ለአንድ ወር የሚቆየው «የመጪው ትውልድ ጤና» አውደ ርእይ እየተካሄደበት ይገኛል። አውደ ርእዩ በሰላሳ ቀናት ቆይታውም ከአንድ መቶ ሺ በላይ ጎብኚዎች እንደሚታደሙበትም የሚጠበቅ ሲሆን በቴክኖሎጂ በተደገፈ መልኩ የሀገሪቱን ጤና ዘርፍ የተመለከቱ በርካታ ሁነቶችም እየተካሄዱ ይገኛሉ፡፡ በርካታ ጎብኚዎችም እየተመለከቱት ይገኛል።

«አውደ ርእዩ በባህላዊ ህክምና ረገድ ያለኝን ምልከታ አሳድጎልኛል » ያለችን በግል ድርጅት ውስጥ የአይቲ ባለሙያ የሆነችው ወይዘሪት ተምኪን አክበር ናት። ወይዘሪት ተምኪን እንዳብራራችው በባህላዊ ህክምና ረገድ በአውደ ርእዩ የቀረቡት ነገሮች ባህላዊ መድሃኒትን በሳይንሳዊ አካሄድ ለህክምናው ማዋል እንደሚቻል ግንዛቤ አስጨብጮኛል። ከዚህ ቀደም ባህላዊ ህክምናና ዘመናዊ ህክምናና አቀናጅቶ መስራት እንደሚቻል ብዙ መረጃ አልነበረኝም። አጠቃላይ አውደ ርእዩ ለጤና ትኩረት አንድንሰጥ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ሲሆን የአዲስ አበባ የሳይንስ ሙዚየምም ተመሳሳይ አውደ ርእዮችን በማዘጋጀት በሀገራችን እየተመዘገቡ ያሉ ለወጦችን እንድናውቅ መሥራት ይጠበቅበታል ስትል ተናግራለች።

በተመሳሳይ በግብርና ሚኒስቴር ሰራተኛ የሆኑት አቶ መላኩ አበራ አውደ ርእዩ እንደ ሀገር በጤናው ዘርፍ ብዙ ለውጥ እየመጣ መሆኑን ለመገንዘብ ችያለሁ። የቀረቡት ነገሮች ቀድመን ጤናችንን እንዴት መጠበቅ እንደምንችል፤ አይበለውና የጤና መታወክ ከገጠመንም ለመታከም ከባህላዊ እስከ ዘመናዊ ልናደርግ ስለሚገባን ነገር በቂ መረጃ የሚያስጨብጥ ነው። እኔ ለማውቃቸው በሙሉ አውደ ርእዩን እንዲታደሙ እነግራለሁ፤ አጋጣሚውን የሚያገኝ በሙሉም መጥቶ ቢጎበኝ ብዙ ያተርፍበታል ሲሉ ተናግረዋል።

በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ድንገተኛና ጽኑ ህሙማን ህክምና ስፔሻላይዝድ ለማድረግ ትምህርቱን በመከታተል ላይ የሚገኘው ዶክተር ሮቤል ስንታየሁ በበኩሉ አውደ ርእዩ ሰፊ በመሆኑና ብዙ ነገር በማካተቱ በአንድ ቀን አይቶ ለመጨረስ እንደሚያስቸግር ይናገራል። በተለይም በጤናው ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎች ደጋግመው ቢመለከቱት ብዙ የሚያገኙበት ይሆናል የሚለው ዶክተር ሮቤል በተለይም በቴክኖሎጂ ረገድ በርካታ አዳዲስ ነገሮች በአውደ ርእዩ ቀርበዋል። በርካታ የፈጠራ ሥራዎችንም አይተናል። የጤና ዘርፉ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ረገድ እየሄደበት ያለው መንገድ ጥሩ ነው። ነገር ግን እዚህ የቀረቡት ነገሮች በሙሉ በመላው ሀገር እንደማይገኙ ይታወቃል። በመሆኑም በሁሉም ቦታ ተደራሽ ማድረግ የሚጠበቅ ሲሆን አውደ ርእዩም ለዚህ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል ሲል ተናግሯል።

«አውደ ርእዩ ህብረተሰቡ ስለጤናው ዘርፍ ለማወቅ ጉጉት እንዳለው አመላካች ነው» ያለችን ደግሞ ከአለርት ሆስፒታል የመጣችውና የህብለ ሰረሰርን ቀዶ ህክምና ማሽን ስታስጎበኝ ያገኘናት ሲስተር ይርጋአለም ከበደ ናት። አውደ ርእዩ ከተከፈ አጭር ቀናት ቢሆኑትም እስካሁን የመጡት ጉብኚዎች በርካታ ናቸው። ብዙ ዝርዝር ነገሮችንም ይጠይቁናል። እኛ ይዘን የቀረብነው በኢትዮጵያ የመጀመሪያውና በምስራቅ አፍሪካም ብቸኛ የሆነ የህብለ ሰረሰርን ቀዶ ህክምና ማሽን ነው።

ከዚህ በፊት በነበረው ህክምና ከአምስት እስከ ስድስት ሴንቲ ሜትር የታካሚው አካል ተከፍቶ ይሰራ ነበር። ሂደቱም ለደም መፍሰስ የሚዳርግና ጊዜ የሚወስድም ነው። አዲሱ ማሽን ግን ቀዶ ጥገናውን ወደ አንድ ሴንቲ ሜትር ዝቅ የሚያደርግ ሲሆን በአንድ ቀን የሚጠናቀቅና ከብዙ ደም መፍሰስ የሚታደግም ነው። እስካሁን አገልግሎት የተሰጠው ለአስራ አምስት ሰዎች ብቻ ነው። ይህንን ስንነግራቸው በርካታ ጎብኚዎች በሀገራቸው ስላለው የህክምና ደረጃ የተሳሳተ ምልከታ እንደነበራቸው ምላሽ ሰጥተውናል። አጠቃላይ አውደ ርእዩ በሀገሪቱ ያለውን የጤና እድገትና የባለሙያዎች ደረጃ የሚያመላክት በመሆኑ በጤናው ዘርፍና በህብረተሰቡ መካከል መቀራረብ ለመፍጠር ይረዳል ስትል ተናግራለች።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የንቅናቄው ስኬት ለመጪው ትውልድም ሆነ ለምንመኘው ሀገራዊ ብልጽግና ወሳኝ ነው!

የአንድን ሀገር እጣ ፈንታ ብሩህ ከሚያደርጉት ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው ትምህርት ነው። ከዚህ የተነሳም ሀገራት ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ይሰራሉ። በሚያገኙት ውጤት መሰረትም ነገዎቻቸው ላይ መናገር የሚያስችል ድፍረት ይጎናጸፋሉ። እንደሀገር የቆሙበትንም መሰረት በየጊዜው እያጸኑ ከትናንት ዛሬ ላይ የተሻለች ሀገር ይገነባሉ።

ዓለማችን ወደ አንድ መንደርነት እየተጓዘች ባለችበት በዚህ ዘመን፣ ዘመኑን በመዋጀት እንደሀገር ዓለም የደረሰችበት ደረጃ ደርሶ አብሮ ለመራመድ የትምህርት ጉዳይ ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ከሆነ ውሎ አድሯል። በተለይም በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገሮች የማደግ መሻታቸውን እውን ለማድረግ በትምህርቱ ዘርፍ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ትልቁ አቅማቸው እንደሆነ ይታመናል።

የእነዚህ ሀገራት አሁነኛ የፖለቲካ ነጻነት ሆነ የነገ ህልሞቻቸው የሚጸኑት ትምህርት ሊፈጥራቸው በሚችላቸው በእውቀት የበለጸጉ ዜጎቻቸው ሁለንተናዊ ተሳትፎ ነው። ለዚህ ደግሞ ለትምህርትና ከሁሉም በላይ ደግሞ ለትምህርት ጥራት ትኩረት ሰጥተው የመንቀሳቀሳቸው እውነታ ብሄራዊ ነጻነታቸውን ከማስጠበቅ ተለይቶ የሚታይ አይሆንም ፤ ብዙ መስዋእትነትን የሚጠይቅ ነው።

ሀገራችንም እንደሀገር ብሔራዊ ክብርን ከማስጠበቅም ሆነ ሀገራዊ ብልጽግናን ለማምጣት ለትምህርት ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የረጅም ታሪክ ባለቤት ናት። በየወቅቱ ሀገሪቱን ያስተዳደሩ መሪዎች በተለይም ዘመናዊ ትምህርትን በማስፋፋት ሀገርን ትልቅ የማድረግ ህልማቸውን እውን ለማድረግ ረጅም ርቀት ተጉዘዋል። የድካማቸውን ያህል ባይሆንም ያገኙዋቸው ውጤቶች የነበራቸው ሀገራዊ ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

በተለይም በአፄ ሀይለስላሴ ዘመን /ከ1930ዎቹ ጀምሮ ዘመናዊ ትምህርትን በመላው ሀገሪቱ ለማዳረስ የተደረጉ ጥረቶችና የተመዘገቡ ስኬቶች፤ ለሀገር ተስፋ የሆነ ትውልድ በማፍራት በተጨባጭ የታዩ ናቸው። ሀገርንም በዓለም አቀፍ መድረኮች ማስጠራት የቻሉ ስመጥሩ የሀገር ባለውለታዎችን በብዛትና በጥራት ማፍራት አስችለዋል።

በደርግም ሆነ በኢህአዴግ ዘመነ መንግስት በትምህርት ጥራት ላይ የነበረው ክፍተት እንዳለ ሆኖ ፤ እንደሀገር ለትምህርቱ ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ተሰርቷል። በተለያዩ ውጪያዊና ውስጣዊ ምክንያቶች በጥራት በኩል የነበሩ ክፍተቶች በጊዜ ሂደት ውስጥ እየሰፉ መጥተው አጠቃላይ የሆነውን ሀገራዊ የትምህርት ስርአት አደጋ ውስጥ ከተውታል። ይህ ደግሞ የአደባባይ ሚስጥር ከሆነ ውሎ አድሯል።

ይህንን ችግር ለዘለቄታው ለመፍታት መንግስት በዘርፉ ሀገራዊ ስትራቴጂ ቀርጾ መንቀሳቀስ ጀምሯል። በተለይም የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ በሁለንተናዊ መልኩ ብቁ የሆነ ሀገር ገንቢ ትውልድ ለመፍጠር የሚያስችሉ ተጨባጭ ተግባራትን እያከናወነ ነው። የፖሊሲ አቅጫዎችን ቀርጾም ወደ ተግባር ለመግባት ሰፊ ዝግጅቶችን በማድረግ ላይ ይገኛል። ከነዚህ ውስጥ አንዱ በቅርቡ የሚጀመረው በህዝባዊ ንቅናቄ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ የማሳደግ ጉዳይ ነው።

ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማር ስኬት ካላቸው ቁመና አንጻር በዓለም አቀፍ ደረጃ በአራት ይከፈላሉ። በደረጃ አራት ላይ የሚገኙት ለመማር ማስተማሩ ሂደት የተሟላ ቁመና ያላቸው ናቸው። በደረጃ አንድ ና ሁለት ላይ የሚገኙት ምንም አይነት የተመቻቸ ቁመና የሌላቸው ሲሆን፤ ደረጃ ሶስት የሚባሉት ብዙም ከነሱ የተለዩ አይደሉም።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በሀገሪቱ ካሉ 49 ሺህ 395 ትምህርት ቤቶች ውስጥ 99 ከመቶ የሚሆኑት ለመማር ማስተማር ውጤታማነት የተቀመጠውን ደረጃ የሚያሟሉ አይደሉም። ደረጃ አራት ላይ የሚገኙት ደግሞ በቁጥር ስድስት ትምህርት ቤቶች ብቻ ናቸው። ይህ ደግሞ ከቁጥር ባለፈ ስለሀገራዊ የትምህርት ጥራት የሚናገረው ብዙ እንደሆነ ይታመናል።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ስለትምህርት ጥራት ማውራት "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" እንደሚባለው አይነት እንደሚሆን አመላካች ነው። ይህንን መሰረታዊ ችግር ሳይፈቱ ስለጥራት ማውራት ትርጉም የሌለው ጮኸት መሆኑ የማይቀር ነው።

ከዚህ ተጨባጭ ሀገራዊ እውነታ በመነሳት መንግስት በቅርቡ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሳደግ የሚጀምረው ብሔራዊ ንቅናቄ የሚኖረውን ሀገራዊ ፋይዳ በሚገባ ተረድቶ መንቀሳቀስ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል።

የንቅናቄው ስኬት ለመጪው ትውልድም ሆነ ለምንመኘው ሀገራዊ ብልጽግና ያለውን ሁለንተናዊ ፋይዳ ተረድቶ በኃላፊነት መንቀሳቀስ በነገዎች ተስፈኛ ከሆነ ዜጋ የሚጠበቅ ነው። ለዚህ ስኬት ደግሞ ሁላችንም ራሳችንን ልናዘጋጅ ይገባል።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ተማሪዎች ያለመጻሕፍት የሚማሩበት ሌላ ዓመት እንዳይደገም

**በየኔነው ስሻው**

### እንደ መግቢያ

በአንድ አገር ውስጥ የሚኖረው እድገትም፣ ውድቀትም በሰው ኃይሉ ላይ ይመሰረታል፡፡ የሰው ኃይሉን በወጉ አስተምሮ ያመራመረ አገር ከችግሮቹ ተሻግሮ ይበለጽጋል። በአንጻሩ ትምህርት የምርምር እና ችግር ፈቺነት አቅም መገንቢያ አውድ መሆን ሳይችል ከቀረ ያ አገር ለፈተናዎች እጁን የሚሰጥ ትውልድ ይፈጥራልና በችግር ውስጥ መዳከር እጣ ፈንታው ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያም እንደ አገር ከትናንት ተሻግራ ዛሬ ላይ ስትደርስ፤ ከዛሬም አልፋ ነገን ስታማትር በዚሁ የሰው ኃይሏ አቅምና ተፈጥሮ በለገሳት ሃብቷ ላይ ተማምና ነው፡፡

ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ ዘመናትን ያስቆጠረው የትምህርት ሥርዓት በየጊዜው እየታደሰና እየተሻሻለ ዘልቋል፡፡ ጊዜ በተለወጠና አዳዲስ ክስተቶች በተፈጠሩ ቁጥር አብሮ ሊለወጥ፣ ሁነቶችንና ክስተቶችን ባማከለ መልኩ ሊዘጋጅ የግድ ስለሆነም፤ ከ2010ሩ አገራዊ ለውጥ ማግስት እንዲለወጡና የሪፎርሙ አካል እንዲሆኑ ከተደረጉ ዘርፎች አንዱ የትምህርት ዘርፉና ሥርዓቱ ነው። በዚህም እንደ አገር አዲስ የትምህርት ፍኖተ ካርታ የተዘጋጀ ሲሆን፤ ፍኖተ ካርታውም በ2015 የትምህርት ዘመን ተግባራዊ መደረግ ጀምሯል፡፡

ይህ ፍኖተ ካርታ እንደ አገር የታዩ የትምህርቱ ዘርፍ ዝንፈቶችን ያቀናል፤ ችግሮችን ያርማል፤ ስብራቶችን ይጠግናል፤ በጥቅሉ በዘርፉ ያሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ቀርፎ ለአገር ሁለንተናዊ እድገትና ብልጽግና የራሱን አበርክቶ የሚያደርግ ትውልድን በእውቀትም፣ በክህሎትም፣ በአመለካከትና በሥነምግባርም አበልጽጎ ለመፍጠር ያስችላል የሚል እምነት ተጥሎበታል፡፡

አዲሱን የትምህርት ሥርዓት ወደ ተግባር ለማስገባት እሱኑ ማዕከል ያደረገ አደረጃጀትና የመማር ማስተማር አውድን መፍጠር ስለሚያስፈልግ በየደረጃው ይሄው ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በዚህም ገሚሱ ዝግጅት ተጠናቅቆ፤ ገሚሱ ደግሞ ከትግበራውም ማግስት በሂደት ላይ ስለመሆኑ ይነገራል፡፡ በሂደት ላይ ካሉ ጉዳዮች እና በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት ውጤታማነት ሚናቸው ጉልህ ከሆኑት መካከል ደግሞ የመማሪያ መጻሕፍት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

መጻሕፍት፣ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ለተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለመምህራንም መሰረታዊ የሆኑ የትምህርት አጋዥ ግብዓቶች ናቸው፡፡ ትምህርትን ያለ መጻሕፍት መማር ማለት፤ እንጀራን ያለ ወጥ እንደመመገብ የሚተናነቅ እውነት ነው፡፡ እንዴት ቢሉ፣ ምንም እንኳን እንጀራ ባማረ መሶብ/ሌማት ቢቀርብም ያለ ወጥ ምሉዕ እንደማይሆን ሁሉ፤ የመማር ማስተማር ሂደትም ትምህርት ቤቶች፣ የመማሪያ ክፍሎች እና ሌሎች ቁሳቁሶች ተውበውና ተሟልተው ቢዘጋጁም ያለመማሪያ መጻህፍት የሚፈለገውን እውቀት ለማስረጽ ፈታኝ ነው የሚሆነው፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ፣ በ2015 ዓ.ም ወደ ትግበራ የገባው አዲሱ ፍኖተ ካርታ/የትምህርት ሥርዓት፤ እሱን ያገናዘበ መጻሕፍት ተዘጋጅተውለትና ታትመው ለተማሪዎች በማድረስ በኩል ችግር ታይቷል፡፡ የትምህርት ዘመኑም መጻሕፍት በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ታትመው ለተማሪዎች ያልደረሱበት፤ ተማሪዎች ከመጻሕፍት ጋር ተነፋፍቀው ያሳለፉበት፤ በዚህም የመማር ማስተማሩ ሂደት ከፍ ያለ ችግር ላይ የወደቀበት፤ ተማሪዎች፣ መምህራንና ወላጆች ጭምር እጅጉን የተፈተኑበት ሆኖ ተጠናቅቋል፡፡

### የትምህርት ጅማሮው ዝግጅት

በኢትዮጵያ ያሉ ትምህርት ቤቶች በኢትዮጵያ የዘመን ቀመር መሰረት መስከረም መጀመሪያው ላይ የመማር ማስተማር ሂደታቸውን እንደሚጀምሩ ይታወቃል፡፡የመማር ማስተማር ሂደታቸውን ሲጀምሩም ከተማሪዎች ምዝገባ ቀጥሎ የሚሆነው ተግባር የመማሪያ መጻሕፍትን ለተማሪዎች ማድረስ ነው፡፡ ይሄ የየዓመቱ የትምህርት ቤቶች ተግባር ቢሆንም የ2015 በጀት ዓመት ግን ከመማሪያ መጻሕፍት አኳያ የተለየ ገጽ ነበረው፡፡

እንዴት? ከተባለም ለዚህ የሚሆኑ አንዳንድ ማሳያዎችን እነሆ፡፡ ዋልታ ኢዜአን ጠቅሶ እና በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የትምህርት ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ዳይሬክተር ወርቅነህ ነጋሳን ዋቢ አድርጎ መስከረም 3 ቀን 2015 ዓ.ም እንደዘገበው፤ በኦሮሚያ ክልል በሁሉም ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ስራ ከማስጀመር ባሻገር፤ የመምህራን ዝግጅት፣ የመማሪያ መጻሕፍት ማዘጋጀትና የትምህርት ቤቶች ዝግጅት ስራ ተከናውኗል፡፡

በዝግጅት ምዕራፉ 34 ሺሕ ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎችን የገነባው ክልሉ፤ በትምህርት ዘመኑ በክልሉ 11 ነጥብ 3 ሚሊዮን (በኋላ ላይ ስምንት ሚሊዮን 28 ሺህ 958 ተማሪዎች በክልሉ በትምህርት ላይ ያሉ መሆናቸው መገለጹን ልብ ይሏል) ተማሪዎችን ለመቀበል የሚያስችል ዝግጅም ተጠናቅቋል፡፡

16 ሺሕ የሚጠጉ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉኝ ያለው የኦሮሚያ ክልል፤ በሁሉም የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት እንደመሆኑ በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት መሰረት የተማሪዎች መማሪያ መጻሕፍት እንደ ቀድሞው የታተሙ መጻሕፍትን ሳይሆን "ሶፍት ኮፒ"ያቸውን ለሁሉም ትምህርት ቤቶች ማድረሱን አሳውቆ ነበር፡፡

እንደ ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ሁሉ፣ በትምህርት ዘመኑ ለሰባተኛ እና ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች 133 ሺህ ያህል መጻሕፍትን በሁለተኛው መንፈቀ ዓመት መገባደጃ ላይ ከማከፋፈል የዘለለ መስራት ያልቻለው የአፋር ክልል ትምህርት ቢሮም፤ ቀሪዎቹ መጻሕፍቶች እስከ ሰኔ መጨረሻ ድረስ ህትመታቸው እንደሚጠናቀቅ ቃል ከመግባት ያለፈ ነገር ማድረግ አልቻለም፡፡ በወቅቱ መጻሕፍትን አትሞ ያላደረሳቸው ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች በሶፍት ኮፒ ለማድረስ ነበር ጥረት ሲያደርግ የቆየው፡፡

የዋና ከተማዋ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮም ቢሆን ከዚህ የተለየ አይደለም። ምክንያቱም፣ መስከረም መጀመሪያ ላይ የመማር ማስተማር ስራውን አስጀመርኩ ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ፣ ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ስራቸውን ከመጀመራቸው ቀደም ብሎ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ስለመከናወናቸው አሳውቆ ነበር፡፡

ለአብነት፣ ጳጉሜን 2014 ዓ.ም የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት የከተማዋ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱን ዋቢ አድርጎ ያወጣው መረጃ እንደሚያሳየው፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ስራ ከመጀመራቸው በፊት የቅድም ዝግጅት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በአዲሱ የትምህርት ስርዓት መሰረት

ወደ 11ኛ ገጽ ዞሯል

# በክልሉ የመማሪያ ክፍሎች ከተማሪዎች ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ አለመሆን ፈታኝ ሆኗል

## - ተማሪዎች በዛፍ ጥላ ሥርና በተጨናነቀ የመማሪያ ክፍል ውስጥ እየተማሩ ነው

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል የተማሪዎች ቁጥር መብዛትና የመማሪያ ክፍል ማነስ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ፈታኝ ችግር እንደሆነ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ገለጸ::

የትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ኪሮስ ጉዑሽ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በክልሉ ከሦስት ዓመታት በፊት የነበረው የተማሪዎች ቁጥር አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ገደማ ነበር:: ሁለት ሺህ 221 የአንደኛ ደረጃ እና 271 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነበሩ:: በአጠቃላይ በ46 ሺህ መምህራን የመማር ማስተማር ሂደት ይከናወን ነበር::

በአሁኑ ወቅት የተማሪ ቁጥር ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ደርሷል ያሉት ኃላፊው፤ ተማሪዎቹ በአንድ ሺህ 377 ትምህርት ቤቶች እየተማሩ እንደሚገኙ ጠቅሰዋል:: አንድ ክፍል ውስጥ እስከ 120 ተማሪ



ዶክተር ኪሮስ ጉዑሽ

ታጭቆ እና ከፊሉ መሬት ላይ ከፊሉ ወንበር ላይ ሆኖ እየተማረ ይገኛልም ነው ያሉት::

በርካታ ተማሪዎችም ዛፍ ስር ተቀምጠው የአስተማሪውን ድምፅ ለመስማት በሚያዳግት መልኩ እየተማሩ እንደሚገኙ ተናግረው፤ አብዛኞቹ መምህራንም ደመወዝ በወቅቱ ሳይከፈላቸው እንደሚሠሩ አስገንዝበዋል::

እንደ ዶክተር ኪሮስ ገለፃ፤ በትግራይ ክልል ከጦርነቱ በፊት የትምህርት ሽፋን የተሻለ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር:: ለመማር ማስተማር ሂደቱ የሚያገለግሉ 300 ሺህ ገደማ የቤተ ሙከራ ማዕከላት፣ የትምህርት መርጃ 30 ሺህ ኤሌክትሮኒክሶች እና 12 ነጥብ አምስት ሚሊዮን የተለያዩ መፃሕፍት ነበሩ:: ሆኖም በጦርነቱ በርካታ ንብረቶች በመውደማቸው አሁን ሁሉም ከነበረበት እጅግ ዝቅተኛ በሚባልበት ደረጃ ይገኛል::

በተፈጠረው ተደራራቢ ችግር ምክንያት ህፃናት ዕድሜያቸው ለቅድመ አንደኛ ክፍል ደርሰው የነበሩ ሳይማሩ አሁን ላይ በሰባትና በስምንት ዓመታቸው ገና ትምህርት ሊጀምሩ መሆኑን ገልጸው፤ ይህ ደግሞ ራሱን የቻለ ችግር ነው ብለዋል:: በተመሳሳይ 12ኛ ክፍል ጨርሰው ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባት ያልቻሉ እንዲሁም ሌላ ሙያ ለመማር ዕድሉ ያላገኙ ተማሪዎች የማህበራዊ ቀውስ ሰለባ ሆነዋል ብለዋል::

በክልሉ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች መካከል 22 በመቶዎች በተፈናቃይ ወገኖች የተያዙ በመሆናቸው በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ይማሩ የነበሩ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዳልተመለሱም ተናግረዋል::

ተማሪዎች ከትምህርት ውጭ ሆነው ያሳለፉት ጊዜ ተስፋ እንዲቆርጡ እንዳደረጋቸውና፤ ወንዶቹ ወደ ስደት ለመሄድ ሴቶችም ወደ አልታሰበ ጋብቻ እንዲገቡ እንደተገደዱ በመጥቀስ፤ ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዳይማሩ የምግብ እጥረት እንዳለም ጠቅሰዋል::

ስለሆነም ችግሩ እንዲቃለል በመንግሥት እና በግብረ ሰናይ ድርጅቶች ለትምህርት ዘርፉ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እገዛ እንዲደረግ ጥሪያቸውን በማስተላለፍ፤ የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ ክልሉ ድረስ በመምጣት እገዛ ላደረጉ እና ባሉበት ሁነው ድጋፍ ለሰጡ አካላት ምስጋናቸውን አቅርበዋል::

# ብሩህ ኢትዮጵያ ውድድር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኩባንያዎች የሚቆጠሩ ናቸው ያሉት ሚኒስትሯ፤ አሸናፊ የሆኑ የሥራ ፈጠራ ሃሳቦችን ወደ ተግባር ለመቀየር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እንደሚሰራ ተናግረዋል፡፡

የተበታተኑና ተቀራራቢ ሃሳቦችን በቅንጅት እንዲሠሩ በማድረግም የተሻለ ውጤት እንዲመጣ በቴክኒክና ሙያ እንዲሁም ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር በመሥራት የተሻለ ውጤት እንዲመዘገብ ለማድረግም መሥራት ይኖርብናል ብለዋል ሚኒስትሯ፡፡

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በቀጣይነትም የፈጠራ ሃሳብ ያላቸውን ዜጎች በቅርበት እንደሚያግዝ ጠቁመው፤ ዕድሉን ያገኙ ወጣቶችም በርትተው በመሥራት ከራሳቸው አልፈው ለሌሎችም አርአያ እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሡ ጥላሁን በበኩላቸው፤ ብሩህ የሥራ ዕድል ፈጠራ ሃሳቦች ውድድር በየዘርፉ ያሉ ቁልፍ ችግሮችን ለመፍታትና የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር የሚችሉ አዳዲስ ሃሳቦች ይዘው የሚመጡ ወጣቶችን ለማበረታታት የተዘጋጀ መሆኑንም ገልጸዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ወጣቶች በየአካባቢያቸው ያሉ እድሎችንና መልካም አጋጣሚዎችን ወደ ሀብት እንዲለውጡና አገራቸውንም እንዲያግዙ እድል የሚፈጥር ነው ብለዋል፡፡

ውድድሩ በ2013 መጀመሩን አስታውሰው፤ በተካሄዱ ሰባት ሀገር አቀፍ እና ክልላዊ ውድድሮች በአጠቃላይ ሁለት ሺ 412 አመልካቾች የተሳተፉ ሲሆን ለ400 ሃሳብ ባለቤቶች ወይም 552 ወጣቶች የቡትካምፕ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በአጠቃላይ ለ 167 ምርጥ ሃሳቦች የአንድ ሚሊዮን 518 ሺህ ዶላር የገንዘብ ሽልማት ተበርክቷል።

ብሩህ ኢትዮጵያ 2015 «ማሠልጠን፣ መሸለምና ማብቃት» በሚል መርህ አንድ ሺህ 137 የክልል እና የዩኒቨርሲቲ አመልካቾችን በሥራ ፈጠራ በማሳተፍና ሃሳባቸውን በማወዳደር አሸናፊ ለሆኑ 50 ተወዳዳሪዎች የአምስት ሺ ዶላር ሽልማት አበርክቷል፡፡

# “ሕዝበ ሙስሊሙ የአረፋ በዓልን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የአማኝ መገለጫ አይደለም::

በበዓሉ ዕለት ወንድሞች እንዳይቸገሩ፣ እንዳያዝኑና ቤተሰቦች እንዳይከፉ የእነሱን ቤት ቀድሞ በመድረስ ችግሮቻቸውን መቅረፍ የበዓሉ መገለጫ ነው::

በዕለቱ እርድ (ኡዱሁያ) የሚከናወን ሲሆን እርዱም በእምነቱ አስተምህሮ መሰረት ለጎረቤት፣ አቅም ለሌላቸውና ለቤተሰብ ይከፋፈላል:: ይህም የሌሎች ችግሮችን በጋራ መካፈል፣ ደስታን በጋራ ማሳለፍና የጋራ የሆነ ማንነትን የመገንባት ሥርዓትን የሚያበረታታ ነው::

በነዚህ መሰል ተያያዥነት ያላቸው የአብሮነት ሂደቶች ውስጥ በመከባበር፣ አንዱ ለሌላው መኖር፣ ለታዛዥነት መዘጋጀትና ተስፋ የማምጣትን እሳቤ በውስጡ የያዘ በዓል መሆኑን ኡስታዝ አቡበከር አስረድተዋል::

የራስን ደስታ ማሟላት የሚቻለው የሌላን ደስታ በመፍጠር ነው ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ ይህን በጠበቀ መልኩ ማክበር የበዓሉ መሰረት መሆኑን አስገንዝበዋል::

በዚህም ሕዝበ ሙስሊሙ በዙሪያው የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን በማገዝና በመርዳት በዓላቸውን ተደስተው እንዲያሳልፉ የእዝነትንና የመረዳዳትን መንፈስ መዝራት የአማኝ ባህሪና ግዴታ መሆኑን ኡስታዝ አቡበከር ገልጸዋል::

እንደ ኡስታዝ አቡበከር ገለፃ፤ በእምነቱ አስተምሮ መሰረት በአረፋ በዓል የሚደረግ ጸሎት (ዱአ) ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ መልኩ ተቀባይነት ስላለው የይቅርታን፣ የእዝነትንና የመረዳዳትን መንፈስ በማዳበር ስለማህበረሰብ፣ ስለችግሮቻችን፣ ሀገር ሰላሟ እንዲጸና እና በመካከላችን ያሉ ነገሮች እንዲስተካከሉ ከምንም ጊዜ በተሻለ መልኩ ፈጣሪን መለመን ያስፈልጋል:: ለዚህም ሁሉም ህብረተሰብ የራሱን ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል::

ከሕይወታችን ባለፈ ለማህበረሰቡ፣ ለህዝቡ ብሎም ለሀገር የሚጠቅምን ነገር በማድረግ ሂደት ውስጥ ትልቁን ድርሻ የምንወጣበት አዲስ ምዕራፍ ለመክፈት በመወሰን በዓሉን ማሳለፍ ይኖርብናል ሲሉ ኡስታዝ አቡበከር መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል::

# በመጪዎቹ ሰባት ዓመታት ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እየተሰራ ነው ያሉት ዶክተር ሀብታሙ፤ ይህን እቅድ ለማሳካት ዓለም አቀፍና ለሀገር ውስጥ አጋር ተቋማት ድጋፍ እንደሚያስፈልግ ለማስገንዘብ ዓላማ ያደረገ ፎረም ነው ብለዋል::

በኢነርጂው ዘርፍ ውጤታማ ስራዎች መከናወናቸውን የገለጹት ኢንጂነር ሀብታሙ፤ 20 ሺ ኪሎ ሜትር የሚደርስ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ተገንብቷል ነው ያሉት::

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ባዮጋዝ በእያንዳንዱ ቤት መድረስ የሚችልና ብልጽግናን ማረጋገጥ የሚያስችል የኢነርጂ አማራጭ ነው:: በኢትዮጵያ በርካታ አርሶ አደሮች ከብቶች አሏቸው:: በየቦታው ተበትኖ የሚቀረው የከብቶች እዳሪን በአንድ ቦታ በማጠራቀም ወደ ባዮ ጋዝ መቀየር የሚቻልበት ሁኔታ በመፍጠር ከብክለት ነጻ የሆነ የማብሰያ ዘዴ እንዲያገኙ ያስችላል:: ለዚህ ደግሞ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅቶች ድጋፍ እንዲያደርጉ ማስገንዘብ አስፈላጊ ነው::

በቂ፣ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው የኢነርጂ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የአየር ንብረት ለውጥና የህዝብ ቁጥር መጨመር ፈተናዎች ናቸው ያሉት ኢንጂነር ሀብታሙ፤ የሚገጥሙ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የመንግሥት፣ የግሉ ዘርፍ፣ የሲቪል ማህበራት ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራርን እንደሚጠይቅ ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ፎረሙ በዋናነት በውሃ ሀብት አጠቃቀም ምን ፍላጎት አለ፣ የመጠጥ ውሃ ተደራሽነት፣ የባዮ ጋዝ አጠቃቀም፣ የኢነርጂ ተደራሽነት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ በመገምገም በቀጣይ ሊሰራባቸው የሚገቡ አሰራሮችን ለመለየት ዓላማ ያደረገ ነው።

ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ አስተማማኝ የውሃ ተደራሽነት፣ የሳኒቴሽንና ሀይጂን ተደራሽነት እንዲኖር ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር እየተሰራ ነውም ብለዋል።

የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ በበኩላቸው፣ አስተማማኝ የንጹህ መጠጥ አቅርቦት ጤናማ ማህበረሰብ እንዲኖር ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው። ከሳኒቴሽን አኳያ ዜጎች የተሻለ የመጸዳጃ ቤት እንዲኖራቸው በማድረግ ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል በሚቻልበት ሁኔታ ላይ በመምከር ጽዱና ምቹ ከባቢን በመፍጠር ጤንነቱ የተጠበቀ ማህበረሰብ መገንባት ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራበት ነው::

የጤና ሚኒስቴር አንዱ ትኩረት አድርጎ የሚሰራበት የማህበረሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ ነው ያሉት ዶክተር ሊያ፣ ንቅናቄ በመፍጠር ለመስራት እቅድ ተይዞ እየተሰራ ነው ብለዋል::

እንደ ዶክተር ሊያ ገለጻ፤ ቤተሰቦች በቀላል ዋጋ ንጹህ የመጸዳጃ ቤት እንዲያገኙ መሰራት አለበት:: የኮሌራ በሽታን ለመከላከል የንጹህ መጠጥ ውሃ ተደራሽነት መኖር አስፈላጊ ነው:: የጤና ሚኒስቴር የማህበረሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ የሳኒቴሽን ተደራሽነት እንዲጎለብት ማድረግ አለበት፤ ለዚህ ስኬታማነት የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተቀራርቦ መስራት አስፈላጊ ነው::

በፎረሙ የውሃ ድጋፍና ሳኒቴሽን ፎረም ስትሪንግ ኮሚቴ ተወካይ አቶ ያዕቆብ መታና እንደገለጹት፤ በውሃ ዘርፉ የተነደፉ የልማት ግቦችን ለማሳካት መንግሥት፣ የግሉ ዘርፍና የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር ወሳኝ ነው።

በፎረሙ የተገኙ ዓለም አቀፍ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ተወካዮች የግብዓት አቅርቦት ችግር ሊቀረፍ እንደሚገባም ጠቁመዋል::

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የክልሉን የግብር አሰባሰብ በዲጅታል ቴክኖሎጂ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

የኦሮሚያ ክልል በርካታ ግብር ከፋዩች ያለው ክልል እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህንን በርካታ ቁጥር ያለው የግብር ከፋይ ለማስተናገድ ተዘርግቶ ስራ ላይ የዋለው አሠራር ግብር ከፋዩን ህብረተሰብ ለተለያዩ እንግልትና አላስፈላጊ ወጪ በመዳረግ የግብር ከፋዩን ቅሬታ ምንጭ ሆኖ ቆይቷል፡፡

ክልሉ በግብር ከፋዩ ሲነሱ የነበሩትን ቅሬታዎች ለመፍታት የሚያስችል አሠራር ለመዘርጋት እየሰራ ይገኛል፡፡ ይህ የግብር አሰባሰብ ሂደቱን በቴክኖሎጂ የታገዘ በማድረግና በማዘመን ለግብር ከፋዩ ተደራሽ፣ ወጪ ቆጣቢና ከብልሹ አሰራር የጸዳ ለማድረግ ሥራ እየሰራ ነው፡፡ ለዚህም በቅርቡ የግብር አሰባሰብ ሂደቱን በዲጂታል ቴክኖሎጂ እንዲፋጠን ለማድረግ የሚያስችለውን የመግባቢያ ስምምነት ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ተፈራርሟል፡፡

የክልሉን ወጪ በክልሉ ገቢ ለመሸፈን በሚደረገው ጥረት የክልሉ ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን ግብር በብቃት ለመሰብሰብ የክልሉ ገቢ ሰብሳቢ አካል በሰለጠነ የሰው ኃይልና በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ሰፊ ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከክልሉ የከሚሰበሰበው ግብር አሰባሰብ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፤ ከክልሉ የተገኙ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ በ2010 በጀት ዓመት የተሰበሰበው የገቢ ግብር ብር 16 ቢሊዮን ሲሆን፣ ይህም በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመር በ2015 በጀት ዓመት ብር 71 ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ደርሷል፡፡ ክልሉ በቀጣዩ ዓመት በ2016 በጀት ዓመት የሚሰበስበውን የግብር ገቢ አሰባሰቡን በማዘመን 130 ቢሊዮን ብር ለማድረስ አቅዷል፡፡

በኦሮሚያ ክልል በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ መስከረም ደበበ እንደሚሉት፤ ክልሉ የታክስ አሰባሰቡን አሁን ካለው አሠራር ይበልጥ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ፣ ወጪ ቆጣቢና ከብልሹ አሰራር የጸዳ ለማድረግ ቁርጠኛ አቋም ይዞ እየሰራ ይገኛል፡፡

ለዜጎች ምቹ የሆነች አገርን ለመገንባት ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ግብርና ታክስ መሰብሰብ ተገቢ ነው የሚሉት ወይዘሮ መስከረም፤ ለዚህም የግብር አሰባሰብ ሥርዓትን ማዘመን አማራጭ የሌለው ተግባር እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ከቴሌ ብር ጋር የአሠራር ሥርዓቱን በማቀናጀት የገቢ አሰባሰቡን ወደ ዲጂታሉ ዓለም በመቀላቀል የገቢ ዘርፉን ለማዘመን መሥራት ደግሞ በእጅጉ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የዲጅታል ቴክኖሎጂ የክፍያ ሥርዓቱ ለገቢ አሰባሰብ በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ነው ወይዘሮ መስከረም የሚገልጹት፡፡ ግብር ከፋዩ ሥራው ቦታ ሆኖ እየሰራ ግብር መክፈል ከቻለ ግብር ለመክፈል የሚያመጣውን ወጪ፣ ጊዜና ጉልበት ይቀንስለታል፤ ጊዜውን በአግባቡ እንዲጠቀም በሥራው ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋል፤ ግብር ለመክፈል ወደ ግብር መክፈያ ማዕከላት ሲመጣ በሚደርስበት ውጣ ውረድ፣ እንግልት፣ በአግባቡ አለመስተናገድና በመሳሰሉት ሳቢያ የሚያነሳቸውን ቅሬታዎች ለመቀነስ እንደሚያስችል ነው ያብራሩት፡፡

የግብር አሰባሰቡ አሰራር ምልልሶች የበዙበት ሆኖ ቆይቷል የሚሉት ኃላፊዋ፤ ግብር ከፋዩ ወደ ግብር መክፈያ ማዕከሉ ሄዶ የሚከፈለውን የግበር መጠን ካወቀ በኋላ ባንክ ከፍሎ እንደገና ተመልሶ ወደ ግብር መክፈያ ማዕከሉ መምጣት እንደሚጠበቅበት ያስረዳሉ፡፡ አሁን ላይ የተዘረጋው ዲጂታል የግብር አከፋፈል ዘዴ ስራ ላይ የቆየውን አሰራር ሙሉ ለሙሉ እንደሚያስቀር ጠቅሰው፣ አልፎ አልፎ ሲታዩ የነበሩ ሌብነትና ብልሹ አሰራሮችንም ያስቀራል ተብሎ እንደሚታመን ይገልጻሉ፡፡ ግብርን በቴሌብር የመክፈል አሠራር ሂደት የግብር ከፋዩን ውጣ ውረድ የሚቀንስ ቀላል፣ ምቹ፣ ወጪ ቆጣቢ የግብር ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ የዲጂታል ክፍያ ሥርዓቱ እስካሁን በክልሉ አራት ዞኖች ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በቴሌብር ታክስና ቀረጥ የመሰብሰብ ሥራ ተጀምሯል። እነዚህ ዞኖች 39 ሺ የሚሆኑ ግብር ከፋዮች ያሏቸው ሲሆን፤ ከ40ሚሊዮን ብር በላይ በቴሌ ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በሸገር ከተማ፣ በአዳማና በቢሾፍቱ እንዲሁም በዋናው መስሪያ ቤት ባሉ ትልልቅ ግብር ከፋዮች በኢ.ብር፣ የኢ.ታክስ እና የኢ.ፋይሊንግ




**የመግባቢያ ስምምነት በተፈረመበት ወቅት፤**

አገልግሎት ተከትሎ የ"ሀ" እና" ለ" ግብር ከፋዩች ስልጠና ወስደው ታክሳቸው በቴሌብር የማሳወቅ ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

‹‹አሁን ላይ ከኢትዮቴሌኮም ጋር የተፈራረምነው ስምምነት በዋናነት ከሐምሌ አንድ ጀምሮ ሰፊውን የግብር ከፋይ የምናገኝበትና በአዲስ በጀት ዓመት የሚሰበሰበው ግብር ተግባራዊ የሚደረግበት ነው›› የሚሉት ኃላፊዋ፤ ግብር ከፋዩ ወደ ሲስተሙ ሲገባ እንዳይቸገር ለማድረግ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመሆን በየቅርንጫፎቻችን ለሚገኙ ሠራተኞች ግብር ከፋዩ በቴሌ ብር በመጠቀም ግብሩን መክፍል እንዳይቸገር ለማድረግ የሚያስችል ስልጠና እየተሰጠ ነው ብለዋል፡፡ እስከ ሐምሌ አንድ ለግብር ከፋዩ ህብረተሰቡ በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች በመጠቀም በቴሌ ብር ግብሩን እንዲከፍል ለማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫና የማስተዋወቅ ሥራ እንደሚሰራም ይገልጻሉ፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ ክልሉ ከ480 ሺ በላይ የሆኑ ግብር ከፋዮች አሉት፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት ከሐምሌ አንድ እስከ ታህሳስ 30 ድረስ ግብር የሚሰበሰብበት የ"ሐ" የግብር ከፋዮች ናቸው፡፡ የግብር አከፋፈል ሂደቱ ሁሉንም ሊያካትት በሚችል መልኩ በየምዕራፍ በመከፋፈል ይካሄዳል፡፡

ዘንድሮ ከተሞች ላይ ሙሉ በሙሉ የግብር መሰብሰብ ሂደቱ በቴሌብር ይፈጸማል፡፡ ከከተሞች በታች ባሉ ወረዳዎች ላይ ግን ግብር የሚሰበሰበው በቴሌብር የሚስተናገዱ ሲሆን፣ ነገር ግን ግብር ከፋዩ ወደ ግብር መክፈያ ማዕከላቱ መጥቶ በኪውአርኮድ እስካን በማድረግ የሚጠበቅበትን የግብር ክፍያ አውቆ በቴሌብር እንዲከፍል በማድረግ ነው የሚፈጸመው፡፡ ይህ አሠራር በሁሉም ዘንድ በተመሳሳይ መልኩ ይሰራበታል ብለዋል፡፡

የሀገራችንን የፋይናንስ ስርዓት በዲጂታል ቴክኖሎጂ በመደገፍ የታሰበውን ሀገራዊ ብልጽግና ለማሳካት የሚደረገውን ርብርብ ጠንካራና አስተማማኝ መሠረት ላይ ለማድረስ መሥራት ያስፈልጋል ያሉት ኃላፊዋ፤ የክልሉ የግብር ከፋዮችና ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ግብር በቴሌ ብር አማራጭ /ፕላትፎርም/ በመጠቀም በቤታቸውና በሥራ ቦታቸው ሆነው ለመክፈል እንዲዘጋጁም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የኢትዮ ቴሌኮም ቺፍ የሞባይል መኒ ኦፊሰር አቶ ብሩክ አድሀና እንዳሉት፤ ግብር ለሀገር፤ ለእድገት ወሳኝ ሚናን ይጫወታል፡፡ ግብር አከፋፈሉ ደግሞ በቴሌ ብር በጣም ቀላል፣ ፈጣን፣ ምቹና አስተማማኝ በሆነ መልኩ የሚፈጸም መሆኑ ሲጨመርበት የግብር አሰባሰቡ ሂደት የበለጠ ይፋጠናል፤ ከፍተኛ ውጤት ይመጣበታል፡፡ ከኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ ጋር ግብርን በቴሌብር በመሰብሰብ የግብር አሰባሰብ ስራውን ለማሳለጥ የሚያስችል አሠራር ተዘርግቷል፡፡

ቴሌ ብር ሁሉን አቀፍ በመሆኑ አገልግሎቱን ለመጠቀም በኤስኤምኤስ፣ በሞባይል መተግበሪያ፣ በተለያዩ ቦታዎች ባሉ ኤጀንቶች እንዲሁም ኮኮብ መቶ ሃያ ሰባት መሰላል (*127#) በመጠቀም ምንም አይነት ቀፎ ሳይመርጥ ዘመናዊ ቀፎ ያለውንም ሆነ የሌለውን ደንበኛ በእኩል የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን ይችላል። በሌላ በኩል በቴሌኮም በኩል ተደራሽነትን ለማስፋት የሚያስችሉ ወደ ጥሪ ማዕከል በመደወል፣ በዌብ ሳይት እና ዌብ ቻት እና በመሳሰሉት አማራጮች በመጠቀም ድጋፍ ማግኘት የሚቻልበት ምቹ ሁኔታም ተፈጥሯል፡፡

ደንበኞች ግብር በቴሌብር ሲከፍሉ ከላይ የተጠቀሱትን የቴክኖሎጂ አማራጮች ሁሉ ተጠቅመን ድጋፍ የምንሰጥበት ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥረናል የሚሉት አቶ ብሩክ፤ በዚህም በአምስት አይነት ቋንቋዎች በአማርኛ፣ በአፋን ኦሮሞ፣ በትግርኛ፣ በሶማሊኛ እና በእንግሊዘኛ በቀላሉ መጠቀም እንደሚቻል ተናግረዋል። እሳቸው እንደሚሉት፤ የኦሮሚያ ክልል ገቢዎች ቢሮ ወደ 409 የግብር መሰብሰቢያ ማዕከላት አሉት፡፡ ክልሉ 23 ከተማዎች፣ 42 ክፍለ ከተማዎች፣ 21 ዞኖችና 323 ወረዳዎች አሉት፡፡ ኢትዮቴሌኮም በእነዚህ ሁሉ አካባቢዎች ከሚገኘው ግብር ከፋይ ግብር ለመሰብሰብ የሚያስችል ሥርዓት እየዘረጋ ይገኛል፡፡ በተለይ በ2016 በጀት ዓመት ለመሰብሰብ የታቀደውን 130 ቢሊዮን ብር ግብር ለመሰብሰብ በቴሌ ብር በማሳለጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

በተጨማሪም በኬላዎች ላይ የሚሰበሰበውን ቀረጥ በቴሌ ብር ለመሰብሰብ የሚያስችል ሥራ እየተሰራ መሆኑንም አቶ ብሩክ ጠቁመዋል፡፡ በምስራቅ አርሲ ሻሸመኔ፤ በምስራቅ ሐረርጌ ቦርደዴ፤ በምዕራብ ሐረርጌ ጎዴ፣ ባቢሊ፣ ደንገጎና ጉሩሱም፤ በደቡብ ምስራቅ ሸዋ ተጂ ኬላዎች ላይ የሚከፈለው የእቃ ቀረጥ በቴሌ ብር እንዲከፈል መደረጉን ጠቁመዋል፡፡ እስካሁን በእነዚህ ቦታዎች ላይ ከ39ሺ በላይ የሚሆኑ ቀረጥ ከፋዮች በቴሌብር አማካይነት የቀረጥ ክፍያቸውን መክፈላቸውንና ከቀረጥ ክፍያው ከ44ሚሊዮን ብር በላይ በቴሌብር መሰብሰቡን ገልጸዋል፡፡

የኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ የታክስ"ሀ "ግብር ከፋዮች ቁጥር 24ሺ፤" ለ "ግብር ከፋዮች 18ሺ ያህል ሲሆኑ "ሐ" የግብር ከፋዮች 456ሺ ግብር ከፋዮች አሉት፡፡ እነዚህ ግብር ከፋዮች ደንበኞች ግብራቸውን በቴሌብር እንዲከፍሉ ተደራሽ ለማድረግ የአጭር የጽሐፍ መልዕክት በመላክ ስልጠናዎችን በመስጠት ወደ ዲጂታላያዜሽን እንዲመጡ ለማድረግ ከገቢዎች ቢሮ ጋር በጋራ እየተሰራ መሆኑን ነው የሚናገሩት፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ የግብር ክፍያን በዲጂታል ዘዴ በቴሌ ብር መክፈል የሚያስገኘው ጠቀሜታ ጊዜን፤ ወጪን ይቆጥባል፡፡ ግብር ከፋዩ ጊዜና ሰዓት ሳይገድበውና ባለበት ሆኖ አገልግሎቱን ማግኘት ያስችለዋል፡፡ ቴሌ ብር ለደንበኞች ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት የክፍያ ደረሰኝ ማጭበርበርን ለማስወገድና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ያስችላል። ዜጎች በቀላሉ የቴሌ ብር የሞባይል መተግበሪያ ወይም *127# አጭር ቁጥርን በመጠቀም ግብርን በመክፈል የክፍያ ማረጋገጫ ደረሰኝ ወዲያውኑ ለማግኘት እንደሚያስችል ገልጸዋል። ቴሌብርን በጣም ቀላል በሆነ መንገድ መጠቀም የሚቻል በመሆኑ አስተማማኝ ነው ብለዋል፡፡

የኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ በአሠራር ሥርዓቱ (በሲስተሙ) አማካይነት ግብር መከፈሉን ወዲያወኑ የሚያወቅባቸው ሁኔታዎች የተቀመጡለት መሆኑን ጠቁመው፤ የግብር አሰባሰብ ሥርዓቱን በቴሌብር የተደገፈ በማድረግ የግብር አሰባሰብ ሥርዓት ማዘመን የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

ከዚህ ባሻገር የክልሉ ገቢዎች ቢሮ በቴሌ ብር ግብር ከመሰብሰቡ አንጻር በዲጂታል ዘርፉ ቀዳሚና ውጤታማ መሆን ያስችለዋል የሚሉት አቶ ብሩክ፤ የግብር ከፋዮችን በዲጂታላይዜሽን ላይ ያላቸውን እውቀት በማሳደግ ግብርን በጊዜውና በወቅቱ በቀላል ዘዴ ለመሰብሰብ የሚያስችል እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

እንደ አቶ ብሩክ ማብራሪያ፤ አሁን ላይ ወደ ዲጂታል ክፍያ ሥርዓት የመግባቱን ሂደት በመጀመር 69 የሚሆኑት የግብር መክፍያ ማዕከላት በቴሌብር ግብር ለመሰብሰብ እንዲችሉ ተደርገዋል፡፡ ለገቢዎች ቢሮ ሠራተኞች ስልጠናዎች የመስጠት ሥራ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመው፤ 285 የሚሆኑ የ‹‹ሐ›› ግብር ከፋዮችን የማሰልጠን ሥራዎች እየሰሩ ናቸው፡፡ በቀጣይ ኢትዮ ቴሌኮም ስልጠናዎች በመስጠት፤ የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም ግንዛቤዎች የመፍጠር ሥራዎችን በመስራት፣ ከገቢዎች ቢሮ ጋር በመሆን በማገዝና በመደገፍ አብሮ እንደሚሰራ ነው የሚናገሩት፡፡

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሪት ፍሬህይወት ታምሩ እንደሚሉት፤ ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ተግባራዊ የተደረገው ቴሌ ብር እስካሁን 34 ሚሊዮን ደንበኞችን ማፍራት ችሏል። ቴሌ ብር በክልሉ የሚገኙ ግብር ከፋዮች ከየትኛውም ቦታ ሆነው በቀላሉ በቴሌ ብር ግብራቸውን ለመክፈል ያስችላል፡፡ ዜጎች ካሉበት ቦታ የገቢ ግብርንም ሆነ የቀረጥ ክፍያቸውን ቀላል፣ ፈጣንና አስተማማኝ በሆነው ቴሌ ብር ቢከፍሉ ጊዜያቸውን ለመቆጠብ ይችላሉ፡፡

ኢትዮቴሌኮም የዲጂታል ሥርዓት በመዘርጋት ሂደት ችግሮች ሲያጋጥሙም መፍትሔ በመስጠት ከተቋማት ጋር ይሰራል ያሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ፤ ኢትዮ ቴሌኮም አስቻይ ሆኖ ተቋማት በሙሉ ተወዳዳሪና ውጤታማ ሆነው ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንድትሆን የአስቻይነትን ሚና እየተጫወተ መሆኑን ነው የጠቆሙት፡፡

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በማሻሻል የትምህርት ጥራትን ማምጣት ይቻላልን?

**ክብረአብ በላቸው**

ትምህርት ለሰው ልጆች ኑሮ ቅልጥፍና፣ ለሀገራት ዕድገትና ልማት እንዲሁም ባህልንና እውቀትን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማሸጋገር እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ስለመሆኑ ብዙ ተብሎለታል። የአንድን ማኅበረሰብ እሴቶችና የተከማቸ እውቀት ማስተላለፊያ መንገድም ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል በትምህርት ላይ የተሠሩ ጥናቶች ያመላክታሉ። ትምህርት ዓለምን ለመለወጥ ቁልፍ መሣሪያ ነው የሚለውንም መርህ የዓለም ሀገራት የሚስማሙበት ጉዳይ ነው፤ ነገር ግን የዓለም ሀገራት በሙሉ ትምህርትን ለለውጥ ተጠቅመውበታል ለማለት ብዙም አያስደፍርም።

የኢትዮጵያ ትምህርት ሥርዓት መንግሥታት በተቀያየሩ ቁጥር አብሮ የሚቀያየር ስለመሆኑም ይናገራል፡፡ አሁን ላይ በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ላይ ለሚታየው ስብራት በርካታ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡

በኢትዮጵያ በአጠቃላይ የትምህርት ዘርፍ ካሉ 47 ሺህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተፈላጊውን "ከፍተኛ ደረጃ" የሚያሟሉት አራቱ ብቻ መሆናቸውን የትምህርት ሚኒስቴር በቅርቡ አስታውቋል። ይህንን ለመለወጥ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል ያለመ ሀገር አቀፍ የትምህርት ዘመቻ በአንድ ወር ተኩል ጊዜ ውስጥ ይፋ እንደሚያደርግም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አስታውቋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ "በኃላፊነት ይሳተፉበታል" የተባለው ይህ ዘመቻ ወላጆችን፣ የቀድሞ ተማሪዎችን እና መምህራንን የሚያሳትፍ ነው፡፡ የትምህርት ቤቶችን ጥራት እና ደረጃ የማሻሻል ሥራ በአምስት ዓመታት ውስጥ ሁሉንም ትምህርት ቤቶች የማዳረስ ዓላማ ያለው መሆኑንም ትምህርት ሚኒስቴር ገልጿል።

የትምህርት ሚኒስቴር ይህንን ያስታወቀው በተወካዮች ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ ላይ የትምህርት ሚኒስቴሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት ነው። እርሳቸው በአጽንኦት ካነሷቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ፤ የትምህርት ቤቶችን ጥራት የሚመለከት ነው።

በሀገሪቱ አጠቃላይ የትምህርት ዘርፍ ባሉ 47 ሺህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ግምገማ ማድረጉን የተናገሩት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፣ በተገኘው ውጤት ላይ ተመስርቶ ትምህርት ቤቶቹ በአራት ደረጃዎች እንደተመደቡ ገልጸዋል። ግምገማው የተደረገው፤ ትምህርት ቤቶች በሚጠቀሟቸው ግብዓቶች፣ በመማር ማስተማር ሂደቶቻቸው እንዲሁም ተማሪዎቻቸው በሚያስመዘግቧቸው ውጤቶች ላይ እንደነበር አመልክተዋል፡፡

በዚህም መሰረት ግምገማ ከተደረገባቸው ትምህርት ቤቶች መካከል "ከፍተኛ" የተባለውን "ደረጃ አራት" ያገኙት፤ አራት ትምህርት ቤቶች ብቻ መሆናቸውን የትምህርት ሚኒስትሩ አስታውቀዋል። የሚፈለገውን ደረጃ ያሟሉት በአጠቃላይ በትምህርት ዘርፍ ውስጥ ካሉት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያላቸው ድርሻ 0 ነጥብ 001 በመቶ መሆኑን የጠቀሱት የትምህርት ሚኒስትሩ፣ ሌሎቹ ትምህርት ቤቶች "የተጠበቀውን ደረጃ ያላሟሉ" መሆናቸውን ለፓርላማ አባላት አስረድተዋል።

በዚሁ ግምገማ በተገኘው ውጤት፤ ከአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 85 ነጥብ 9 በመቶ የሚሆኑት "ፍጹም ከደረጃ በታች" መሆናቸው መረጋገጡን ፕሮፌሰር ብርሃኑ ተናግረዋል። ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ደግሞ 70 ነጥብ 9 በመቶ የሚሆኑትም በተመሳሳይ ሁኔታ ከሚጠበቀው "ደረጃ በታች" ማስመዘገባቸውን አክለዋል። እነዚህ ትምህርት ቤቶች፤ በግምገማው በ"ደረጃ አንድ" እና "ደረጃ ሁለት" ምድብ የተቀመጡ መሆናቸውንም አብራርተዋል።

ትምህርት ሚኒስቴር የእነዚህ ትምህርት ቤቶችን ደረጃ እና ጥራት ለማሻሻል፤ "ህብረተሰቡን በማስተባበር" ጥገና እና እድሳት እያደረገ መሆኑን ፕሮፌሰር ብርሃኑ ተናግረዋል። በዚህ አይነት መልኩ 8 ሺህ 700 ገደማ ትምህርት ቤቶች ጥገና እና እድሳት እንደተደረገላቸውም በማሳያነት ጠቅሰዋል።



ዶክተር አማኑኤል ኤርሞ



ዶክተር እንዳለው ፋፋ

የትምህርት ባለሙያ እና በኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ዶክተር አማኑኤል ኤሮሞ እንደሚናገሩት፤ የትምህርት ጥራትን አመላካች ነው የሚባለው የተማሪዎች ውጤት ነው። በተማሪዎች ውጤት ላይ ደግሞ ከፍተኛ ሚና ያላቸው አራት አካላት ናቸው ይላሉ። ተማሪው ፣ወላጅ ፣መምህር ርዕሰ መምህር እና የትምህርት ቤቱ ምቹ ሁኔታ ናቸው፤ እነዚህ አካላት ናቸው በተማሪ ትምህርት ጥራት ላይ ትልቅ ሚና ቀድመው የሚጫወቱት ሲሉ ያክላሉ።

ዶክተር አማኑኤል፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሰሩ ጥናቶችን ዋቢ አድርገው እንደተናገሩት፤ የትምህርት ጥራትን ለማምጣት በትምህርት ቤቶች ውስጥ የጋራ ርዕይ መኖር አለበት፤ ይህንን ርዕይ የሚቀርጸው ደግሞ አመራሩና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ነው። በዚህ ሂደት ደግሞ ዋናው ከርዕሰ መምህር እስከ ትምህርት ክፍል ያሉ አመራሮች ቁርጠኝነት ነው። የእነርሱ ቁርጠኝነት ወሳኝ ነው። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ የትምህርት አመራር እውቀት ያላቸው ናቸው ወይ ትምህርት ቤቶችን እየመሩ ያሉት የሚለው በራሱ የሚያጠያይቅ ነው።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ባለፈው ሥርዓት በየትምህርት ቤቶቹ ሲመደቡ የነበሩ ርዕሰ መምህራን ፖለቲካዊ በሆነ መንገድ ነው፡፡ እነርሱ ደግሞ ከሙያ ብቃታቸው አንፃር ሲታዩ በትምህርት አመራር እውቀት እና ልምድ ያላቸው አይደሉም፡፡ እነርሱም ቢሆኑ በየጊዜው ይለዋወጣሉ፤ በዚህ መልኩ እየተሰራ ለውጥ መጠበቅ የማይታሰብ ነው።

በሌላ በኩል በአመራሩ፣ በርዕሰ መምህሩም ሆነ በመምህሩ ላይ ተጠያቂነት መኖር አለበት፤ ማለትም ጥሩ ሥራ ከሰሩ መሸለም ከደረጃ በታች ሥራ ከሰራ ደግሞ መጠየቅ አለባቸው፡፡ አሁን በእኛ አካሄድ ይህ አሰራር የለም፤ ጠቅላላ ተማሪ ቢወድቅም እንዴት ሆነ ተብሎ ርዕሰ መምህሩ አይጠየቅም፡፡ በጠንካራ ሥራ ደግሞ ሁሉንም ተማሪ ማሰለፍ ቢችልም የሚያበረታታ አካሄድ የለም፡፡ ይህ አካሄድ መስተካከል ይገበዋል ብለዋል።

በአርሲ ዩኒቨርሲቲ የሥርዓተ ትምህርት እና ፖሊሲ ጥናት መምህር እንዲሁም በዘርፉ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር እንዳለው ፋፋ በበኩላቸው፤ በአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ጥራት ለማምጣት አሰራሩ በምን ሁኔታ ነው የሚያልፈው የሚለውን ማገናዘብ ያስፈልጋል ብለዋል፤ በአጭር ጊዜ የሚመጣ ለውጥ የለም፤ ስህተቱ ምን ነበር ብሎ ጥናት እና ምርምርን መሰረት አድርጎ የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥ ይገባል ሲሉም ጠቅሰዋል፡፡

እርሳው እንደሚናገሩት፤ በሌላ በኩል በ1987 ዓ.ም የፀደቀው የኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲ መሰረት ያደረገው ጥራት ላይ አልነበረም፡፡ በወቅቱ ተደራሽነት ስላልነበረ ይህንን ለመፍታት ሰፊ ሥራዎች ተሰርተው በትምህርት ቤቶች ብዙ ሀብት ወጥቷል፡፡ ነገር ግን የጥራቱ ጉዳይ የተዘነጋ እንደነበር ተናግረዋል።

ተደራሽነቱን እና ጥራቱን ደግሞ አንድ ላይ ማስኬድ ከባድ እንደነበር የሚናገሩት ዶክተር እንዳለው፣ አሁን ላይ ሙሉ ለሙሉ ጥራት የለም ማለት እንደማይቻል አመልክተዋል፡፡ የተደራሽነቱን ያህል ጥራት ማምጣት አልተቻለም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የተማሪው ቁጥር ብዙ በመሆኑ አንዱ ነው፡፡ ይህን ሁሉ ተማሪ በክህሎትም በእውቀትም ብቁ ለማድረግ ሁኔታዎች ምቹ አይደሉም፡፡

ዶክተር እንዳለው እንደሚገልጹት፤ አሁን የምንሰራው ነገር በዘለቄታ ምን ውጤት ያመጣል የሚለውን ከግምት ማስገባት ይገባል፡፡ ወደኋላ የሚመልሰን እንዳይሆንም መጠንቀቅ አለብን፡፡ በተመሳሳይ ተደራሽነቱንም የሚገታ እንዳይሆን ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ ሆኖ ወደ ሥራ ቢገባ ውጤታማ ያደርጋል።

የአንድ ትምህርት ቤት ማህበረሰብ ሁልጊዜ ከተማሪው ከፍተኛ ውጤት በመጠበቅ መስራት አለበት፡፡ በሌላ ጎኑ ትብብር እና ግንኙነት በመፍጠር በጋራ መሰራት መቻል አለበት፡፡ በትምህርት ቤቶች ትልቁ ቢዝነስ የሚባለው ሥርዓተ ትምህርቱ፣ የመማር ማስተማር ሂደቱ፣ የተማሪዎች የመማር ሂደት በየጊዜው መገምገም ሲሆን፣ እነዚህ ተቀናጅተው በየዕለቱ መሰራት አለባቸው የሚሉት ደግሞ ዶክተር አማኑኤል ናቸው።

ተከታታይ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደትን መከታተል ይገባል የሚሉት ዶክተር አማኑኤል፣ ይህ ደግሞ ትኩረቱን ማድረግ ያለበት በክፍል ውስጥ ምን እየተሰራ ነው? የሚለው ላይ ነው ሱሉ ይናገራሉ፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የጠቀሱት፤ ትልቁ ቁምነገር ያለው በመምህሩ፣ በተማሪውና የመማሪያ መጽሐፉ ላይ ስለሆነ ነው ይላሉ፡፡ ሌላው የመምህራን አቅም መገንባትና ሙያ መሻሻል ላይ ትኩረት መደረግ አለበት፤ መምህራን ይህን የሙያ አቅማቸውን ሲያጎለብቱ ደግሞ አጀንዳቸው መሆን ያለበት የተማሪ ውጤት ላይ መሆን ይኖርበታል ሲሉም ያክላሉ።

ሌላው አጋዥ ሁኔታዎች የሚባሉት ደግሞ አሉ ያሉት ዶክተር አማኑኤል፣ ቤተ መጻሕፍት፣ ቤተ ሙከራ እንዲሁም ምቹ የመማሪያ ክፍሎች እንደሚያስፈልጉ ይናገራሉ፡፡ የወላጆች የነቃ ተሳትፎም የግድ ነው፤ ወላጆች ስለልጆቻቸው ጉዳይ ከትምህርት ቤቱ ጋር በጋራና በቅንጅት መስራት መቻል አለባቸው፡፡ ይህ ካልሆነ ውጤታማ መሆን እንደማይቻልም ይናገራሉ፡፡

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ዋናው አሁን መሰራት ያለበት በትምህርት አመራሩ፣ በመምህሩ ብቃት፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ እና በወላጆች ተሳትፎ ላይ ነው፡፡ ተማሪዎች ለትምህርት ያላቸው ፍላጎት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ጥቂት የማይባል መምህር ደግሞ ተማሪውን ውጤታማ አደርጋለሁ የሚል ሞራል የለውም፡፡ የዚህ ምክንያት ደግሞ በቂ ደመወዝ እየተከፈለው አለመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህን ጉዳዮች ለማሻሻል ከተሰራ በትክክል ለውጥ ማምጣት ይቻላል፡፡

የትምህርት ቤቶችን ደረጃ መለካት ያለብን ባላቸው ግብዓት ብቻ መሆን የለበትም፡፡ ቅድሚያ መሰጠት ያለበት ምን አይነት ጥሩ መምህር አለ በሚለው ላይ ነው፡፡ ግብዓትን በማሟላት ብቻ የትምህርት ጥራት አይመጣም። ዋናው እና ትልቁ ግብዓት ብቃት ያለው መምህር በመሆኑ እዚህ ላይ በትኩረት መስራት እንደሚገባ ዶክተር አማኑኤል ተናግረዋል፡፡

የተማሪዎችን የዕውቀት ደረጃ ለማሻሻል ከተፈለገ ራሳቸው ተማሪዎች የሚማሩትን ጉዳይ ጠንቅቀው ትምህርታቸውን መከታተል እንዲችሉ ለማድረግ መስራት እንጂ እንዲሁ ከክፍል ወደ ክፍል ለማለፍ የሚማሩት መሆን የለበትም የሚሉት ደግሞ ዶክተር እንዳለው ሲሆኑ፣ ተማሪው እስከ አስራ ሁለተኛ ባለው የትምህርት እርከን ውጤታማነቱን እያረጋገጠ የሚሄድ መሆን እንዳለበት አመልክተዋል፡፡ በዚህ ሒደት የመማር ማስተማሩ ተግባር የተሟላ ይሆን ዘንድ ትምህርት ቤቶች ትክክለኛ ግብዓትን ያሟሉ መሆን እንዳለባቸውም ጠቅሰዋል፡፡

ሌላው ዶክተር እንዳለው አፅንኦት የሰጡት ጉዳይ፤ የመምህራን የስልጠና ደረጃ ምን ያህል ነው? ያመጣናቸውስ እንዴት አሰልጥነን ነው የሚለው ላይ ነው፡፡ ቅርብ ጊዜ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ከሆነው ኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ውጭ ትምህርት ላይ ትኩረት አድርጎ በዘርፉ ብቁ የተማረ የሰው ኃይል ማፍራት የሚችል ተቋም የለም፡፡ ከአመታት በፊት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በመምህራን ስልጠና ፕሮግራም ላይ በስፋት ነበሩ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ስልጠና የሚያገኙት የመምህርነት ብቻ ሳይሆን የሥርዓተ ትምህርት ጥናት፣ የምዘና እና ክትትል ሂደት፣ የማጥናት ሁኔታም ነበር፡፡ በዚህም ስልጠና የተሻለ እውቀት ይዘው ይወጡ ነበር፡፡ አሁን ያለው የስልጠና አካሄድ የሚመጥን እና የመምህራንን አቅም የሚያሳድግ አይደለም፡፡

የትምህርት በጀትን በተመለከተ የሥራ ማስኬጃ ተብሎ የሚመደበው እንደሚታሰበው ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ለመስጠት አይደለም፡፡ በትምህርት ቤቶች ግብዓት የለም፤ ይህ ከሌለ ደግሞ አሰራር አይኖርም። አሰራር ሳይኖር ደግሞ ጥራት አይመጣም፡፡ ይህንን በተወሰነ መልኩ እንኳ ለመቅረፍ ከላይ እስከታች የበጀት ምደባውን ጨምሮ ያልተማከለ መሆን አለበት፤ ተማሪውን የሚስብ ከባቢያዊ ሁኔታ ለመፍጠር መሰራት የግድ የሚባልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ብለዋል፡፡

እንደ እርሳቸው አባባል፤ ሌላው ትልቁ ጉዳይ የትምህርት ቤቶች ከባቢያዊ ሁኔታ ነው። አዋኪ ከሆኑ ነገሮች የፀዱ ናቸው ወይ የሚለውን ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ከትምህርት ጋር በፍጹም አብሮ መሄድ የማይችሉ ነገሮች የትምህርት ቤቶችን ዙሪያ ሞልተዋል። እነዚህን ሁኔታዎች የአካባቢውን ማህበረሰብ፣ የመንግሥትና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ካልሆነ የምናስበው ውጤት ሊመጣ አይችልም፡፡

የቤተሰብና የወላጆች ሚና ትልቅ ሊሆን ይገባል የሚሉት ዶክተር እንዳላው፣ አንደኛ የልጆቻቸውን ትምህርት መከታተል በሁለተኛ ደረጃ ከትምህርት ቤቶች ጋር መስራት እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡በትምህርት ቤቶች የጎደሉ ነገሮችን ለማሟላት በትብብር መሥራት መቻል አለባቸው፡፡ በየደረጃው ያሉ አመራር አካላት ኃላፊነት ወስደው ተከታታይነት ባለው መልኩ ለነገ ትውልድ በመጨነቅ ሊሰሩ እና የትምህርት ነገር ግድ የሚላቸው ሊሆኑ ይገባል ብለዋል።

ምሁራኑ እንደተናገሩት፤ የትምህርት ቤቶች ደረጃ መሻሻሉ ጠቃሚነቱ የሚያከራክር አይደለም ፤ነገር ግን በምን መልኩ የሚለው በጥናት ላይ ተመስርቶ መሆን አለበት። በሌላ በኩል ከላይ እስከ ታች ያለው የትምህርት አመራር በዘርፉ የሰለጠነ እና እውቀት ያለው ሆኖ በጥንቃቄ መደራጀት አለበት፡፡ ይህ አሠራሩን ውጤታማ ያደርገዋል፡፡

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ‹‹የእናቶች ችግር ሲቀረፍ ልጆች ህልም ኖሯቸው ያድጋሉ››

ጋዜጠኛ ዙቤይዳ አወል



**ሰላማዊት ውቤ**

ወላጆች ለልጆቻቸው እኩል ዕድል እየሰጡ ማሳደጋቸው ልጆች የየራሳቸው የወደፊት ህልም እንዲኖራቸው ያደርጋል ብለው ያስባሉ። የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት (ኢቢሲ) የማህበራዊ ጉዳዮች አርታኢ ዙቤይዳ አወልም እናቷ ያሳደጓት በዚህ መንገድ ነው።

ዙቤይዳ አወል ‹‹ብዙ ልጆች የየራሳቸው የወደፊት ህልም አላቸው። ዶክተር ፣መምህር፣ፓይለት፣ፖሊስ እያሉ ወደፊት የሚሆኑትን ከወዲሁ የሚናገሩት ለዚህ ነው›› ትላለች። እርሷም ለአቅመ ሄዋን ከደረሰች ጀምሮ ልጆች የራሳቸው ህልም ኖሯቸው እንዲያድጉ ለማስቻል እናቶቻቸውን ለመደገፍ በግሏ ስትጥር ቆይታለች።

በተለይ በኢቢሲ ማህበራዊ ጉዳይ ላይ መሥራት ከጀመረች አንስቶ በሥራ ላይ የሚገጥሟት ከእናቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች የበለጠ ትኩረት ሰጥታ እንድትሰራ አድርጓታል። ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚገጥማትን ሁሉ በፌስቡክና በሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች በማጋራትና ሌሎችን በማሳተፍ ጭምር ይህን በጎ ተግባር ለሁለት ዓመታት ስትከውን ቆይታለች። የእርሷ በእናቷ መልካም ስብእና መቀረፅ በዘር፤ ቀለምና ሃይማኖት ሳይለዩ የተቸገሩ ሰዎችን በመርዳት የበጎ ተግባር ተምሳሌት የሆኑትን ማዘር ትሬዛን እንድትወድ አድርጓታል።

ዙቤይዳ ጋዜጠና ብቻ ሳትሆን የማህበራዊ ሚዲያ አንቂም ናት። በዚህ ዓመትም ቢያንስ ኢትዮጵያዊት ማዘር ትሬዛ በመሆን በጎ ተግባሩን በተቋም ደረጃ ማስጀመር አለብኝ ብላ በማሰብ ‹‹እናት ዙበይዳ›› የተሰኘ የበጎ አድራጎት ድርጅት አቋቁማለች። በዚህ ድርጅት በርካታ ልጆች የራሳቸው ህልም እንዲኖራቸው፣ በርካታ እናቶችም ልጆቻቸው የራሳቸው ህልም ኖሯቸው እንዲያድጉ ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል። ለእናቶች በሚደረገው ድጋፍ ውስጥ ልጆችም ተጠቃሚ ሆነዋል። ስማቸው ለዚህ ፅሁፍ ሲባል የተቀየረው የአስር ዓመት ታዳጊ ህፃን ዮናስ አበበና እናቱ ወይዘሮ አስምረት ጋሻው ደግሞ የዚህ ድጋፍ ተቋዳሽ ናቸው።

ወይዘሮ አስመረት ሁለት መንታ ልጆች እንዳሏት ትናገራለች። ልጇቿ በቤት ውስጥ ያለባትን ችግር እንደሚያዩና በተለይ ልጇ ዮናስ ‹‹እኛ ልጆችሽ ቶሎ አድገንና ተምረን ሥራ በመያዝ እናሳልፍልሻለን ፤ቆንጆ ቤትም እንገዛልሻለን›› እያለ ተስፋ እንደሚሰጣት ነው የምትገልፀው። የአስር ዓመቱ ልጇ ዮናስ በጣም ጎበዝ ተማሪ እንደነበር ሆኖም በሚኖሩበት አዲስ አበባ አሜሪካ ጊቢ አካባቢ በድንገት ተገዶ እንደተደፈረባት በሃዘን ትገልፃለች። በወቅቱ ሕክምና ቢያገኝም የአካል ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የስነ ልቦና ጉዳት እንደደረሰበትም ታስረዳለች። በዚህም ትምህርቱን ለማቋረጥ ተገዷል። ይህንንም ተከትሎ ወደ ጎዳና መውጣቱን ወይዘሮ መሰረት ታስታውሳለች።

“ከብዙ ፍለጋ በኋላ ሜክሲኮ አየነው ብለው ሰዎች ነገሩኝ። ኃይለኛ ዝናብ እየዘነበ በእኩለ ሌሊት ጎዳና ላይ የተኙ ልጆችን በሙሉ እየገለጥኩ ስፈልግ ቆይቼ በመጨረሻ አገኘሁት›› ትላለች ወይዘሮ መሰረት በሃዘን ስሜት ውስጥ ገብታ። በዚያ ሌሊት እሱን ፍለጋ ወጥቼ ሳገኘው ደንግጦ ጭለማውን ለምን እንዳልፈራሁ ጠይቆኝ ተስፋ በመቁረጥ በቀላሉ እሺ ብሎ አብሯት ወደ ቤት ለመመለስ ፍቃደኛ እንዳልነበረም። በኋላ ላይ ግን ብዙ አባብላና ለምና ወደ ቤት እንዳስገባችው ትናገራለች።

‹‹እንቢ ሲለኝ ምርር ብዬ ሳለቅስና ወደቤት የማይመለስ ከሆነ እራሴን እንደማጠፋ ስነግረው ነው አብሮኝ የተመለሰው›› ትላለች ወይዘሮ መሰረት። ይሄን ያልኩት ለጊዜው ወደ ቤቱ እንዲመለስልኝ ለማባበል ብቻ ሳይሆን በርግጥም ጉዳቱ ተሰምቶኝም ጭምር ነው ስትል ትገልፃለች።

ወይዘሮ መሰረት እንደምትናገረው፣ ልጇ ዮናስ ከመደፈሩ በፊት ሻይ በመሸጥ ነበር እሱንና መንትያ እህቱን የምታሳድጋቸው። ልጇ ላይ ጉዳት ከደረሰ በኋላ ግን ሥራውን አቁማ እሱን ፍለጋ መባዘን ሆነ ሥራዋ። በዚህ ወቅት ሻይ የምታፈላበትና የምትሸጥበት ማንቆርቆሪያና ብርጭቆዎች እንዲሁም ሌሎች ቁሳቁሶችም ተዘርፈውባት ነበር። አሁን ግን የዮናስ እናት የ‹‹እናት ዙቤይዳ›› በጎ አድራጎት ድርጅት ባደረገላት የፔርሙስ፣ የሌሎች ቁሳቁሶችና የመነሻ ካፒታል ድጋፍ አሜሪካን ጊቢ አካባቢ ሻይ እያፈላች በመሸጥ ልጆቿን እያሳደገች ትገኛለች።

“ቀበሌ የሰጠኝና የምኖርበት ቤት እጅግ ከመጥበቡም በላይ አይመችም” የምትለው ወይዘሮ መሰረት፤ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ዙቤይዳ ‹‹ቤታችን ከጎዳና አይሻልም፤ ጎዳናም ኖርኩ እቤት ውስጥ ልዩነት የለውም›› የሚለውን ልጇን እናትህን ትተህ የትም መሄድ የለብህም ስለዚህ በቤት ውስጥ ከእናትህና ከእህትህ ጋር መኖር ይሻልሃል›› ብላ እንደመከረችው ታስረዳለች። ይሁንና ልጇ ዮናስ ከደረሰበት የስነ ልቦና ጉዳት በቶሎ አገግሞ ትምህርቱን መቀጠል እንዳልፈለገ ትገልፃለች። ካልሲ በመሸጥ እናቱን መርዳት እንደሚፈልግ ተናግሮ እንደነበርም ታስታውሳለች። በዚህም ይህን ሥራ ለመሥራት የሚያስችለው የገንዘብ ድጋፍ በድርጅቱ በኩል ተደርጎለት ወደ ሥራ መግባቱን ትናገራለች።

ልክ እንደ ወይዘሮ መሰረት ሁሉ ወይዘሮ ብርቱካን ከበደም /ለዚህ ፅሁፍ ስሟ የተቀየረ/ በድርጅቱ በኩል ድጋፍ የተደረገላት ናት። እርሷ እንደምትለው ቀደም ሲል ሦስት ልጆቿን ታሳድግ የነበረው የተለያዩ ቁሳቁሶችን ጎዳና ላይ በመሸጥ ነበር። ሆኖም በተደጋጋሚ ደንብ አስከባሪዎች እቃዎቿን ስለወሰዱባት ለኪሳራ ተዳርጋ ስራውን ትታለች። ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ›› እንዲሉ ዓይኗን ታማ እይታዋ ተጋርዶ በህመም ስትሰቃይ ቆይታለች።

‹‹በህመሜ ከኔ ይልቅ ልጄ የበለጠ ይሳቀቅ ነበር። ብዙ ጊዜ አዝኖ አጠገቤ ኩርምት ብሎ ይቀመጥና ሲያድግ ዓይኔን እንደሚያሳክመኝና ዳግም እንደማልታመም ይልፅልኝ ነበር›› ትላለች ወይዘሮ ብርቱካን። እንኳን ለዓይኗ መታከሚያ ይቅርና ለልጆቿ የምታበላው የዕለት ጉርስ እስከማጣት ደርሳ እንደነበርም ትጠቁማለች።

አሁን ላይ ግን ያ ጊዜ አልፎ ወይዘሮ ብርቱካን በልጇ አማካኝነት ያገኘቻት ዙባይዳ ዓይኗን እንድትታከም አድርጋላታለች። የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ሐኪሞች በየአይኗ ውስጥ በቅሎ የነበረውን ፀጉር ለቅመው ስላወጡላት ከህመሟም ተፈውሳለች። ደንብ አስከባሪዎች ከዚህ በፊት ወስደውባት የነበሩትን አይነት ‹‹ሌርገንዶ›› ጫማዎች ዙበይዳ መርካቶ ወስዳ ገዝታላት እየሸጠች ትገኛለች። ልጇም ደስ ብሎት ትምህርቱን እየተማረ ነው።

ዙበይዳ ስለ ወይዘሮ ብርቱካን እንደምትናገረው ክፍል ውስጥ ሲማር አንድ መምህር ‹‹ስታድጉ ለወላጆቻችሁ የምታደርጉላቸውን ነገር ንገሩኝ›› ብሎ በጠየቀው ጥያቄ ምክንያት አግኝታዋለች። ‹‹እናቴን ዓይኗን አሳክማታለሁ›› የሚል መልስ ለመምህሩ እንደመለሰም ተረድታለች። ቃለ መጠየቅ ስታደርግ ‹‹ሳድግ ለእናቴም፤ ለእኔም ጫማ እገዛለሁ›› ያላት ሌላም ልጅ ገጥሚታል።

ነገር ግን የእነዚህ ልጆች ህልም እናትን ከማሳከምና ጫማ ከመግዛት አልፎ አውሮፕላን አብራሪ ሆነው እያንሸራሸሩ ሀገር እስከ ማስጎብኘት፣ ቪላ ቤት እስከ መግዛትና የሀገር መሪ እስከመሆን መዝለቅ እንዳለበት ትጠቁማለች። በድህነት ምክንያት በተለይም በቤት ውስጥ ባለ ችግር ሃሳብ ስለሚይዛቸው አብዛኞቹ ልጆች በትምህርታቸው ጎበዝና ውጤታማ እንዳልሆኑና ጎበዝ የነበሩ ልጆች ውጤታቸው ቀስ በቀስ እየቀነሰ እንደሚሄድም ትጠቅሳለች።

የድርጅቱ ዓላማም በኢኮኖሚ ዝቅተኛ የሆኑ እናቶች ቢያንስ በልቶ ማደር የሚያስችልና ትንሽም ቢሆን ገቢ እንዲኖራቸው፤ ልጆቻቸውም የየዕለት ችግር ከማሰብ እንዲወጡ የሚያደርግ አነስተኛ ድጋፍ ማድረግ መሆኑን ታስረዳለች። በዚህ ድጋፍም ልጆቹ ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ እንደሚታሰብም ትጠቅሳለች።ባሎቻቸው ሞተው ወይ ተለይተዋቸው ብቻቸውን ልጆቻቸውን የሚያሳድጉ እናቶች እንዲሁም አካል ጉዳተኛ ልጅ ኖሯቸው ለልጆቻቸው ሲሉ ሥራቸውን ትተው ቤት ውስጥ ከልጆቻቸው ጋር ለመቀመጥ የተገደዱ እናቶች በድጋፉ ተጠቃሚ መሆናቸውንም ትገልፃለች። ልጆቻቸውን ለማሳደግ የሚቸገሩ እናቶች በተለይ አካል ጉዳተኛ ልጆች የያዙ ከመሆናቸውም በላይ ተደራራቢ ጉዳት እንደሚደርስባቸውም ዙቤይዳ ታስረዳለች።

አብዛኞቹ ልጆቻቸው የፓንፐርስ ድጋፍ የሚፈልጉና ራሳቸውን ችለው የማይንቀሳቀሱ ናቸው። ቢያንስ የልጆቻቸው ተፈጥሯዊ ጉዳት እንዳለ ሆኖ በኢኮኖሚ ራሳቸውን ችለው እናቶቻቸው ልጆቻቸውን የሚንከባከቡበት እነሱ የማይበሳጩበት፤ ልጆቻቸው ተስፋ የማይቆርጡበት እንዲሁም የራሳቸው ህልም እንዲኖራቸው ማድረግ የድርጅቱ ዓላማ ነው።

ዙበይዳ እንምትገልፀው በዚህ ዓመት መጨረሻም ድጋፍ የሚደረግላቸው ሃያ እናቶች ተመርጠዋል። የተወሰኑት በሥራ አጋጣሚ የተገኙ ሲሆኑ፤ አብዛኞቹ ደግሞ ልጆቻቸው ትምህርት ቤት ገብተው የሚማሩ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ አካል ጉዳተኞችም ይገኙበታል። በአብዛኛውም መምህራኖቻቸው ችግራቸውን በሚገባ የሚያውቁላቸው ወላጆች ናቸው ለእርዳታ የተሰባሰቡት። ለነዚህ ሃያ እናቶች መሥራት የሚችሉትን ሥራ እንዲሰሩ መነሻ ካፒታል በመስጠት ልጆቻቸውን በተሻለ ሁኔታ እንዲያሳድጉና ኢኮኖሚያቸውን እንዲያሻሽሉ ይደረጋል።

‹‹የእኛ ልጆች ህልም አላቸው፤ የእነዚህ እናቶች ልጆች ከእኛ ልጆች ጋር እንደማይደጋቸውና የነገ ሀገር ተረካቢ እንደመሆናቸው ለልጆቻችን የምናስረክባት ኢትዮጵያ የነዛም ልጆች ኢትዮጵያ ናት ብለን ማሰብ አለብን›› የምትለው ዙበይዳ፤ ዝቅተኛ ኑሮ ያላቸው እናቶች ልጆች ሀገር ኢትዮጵያ እንጂ ሌላ ሀገር ባለመሆኗ ሀገሪቱ ለእነሱ ዕድል እየሰጠች፤ ኃላፊነት እንዳለባት እያሳየች ያሳደገቻቸው ሀገር እንዲመስላቸው ተደርጎ እንዲያድጉ እንደምትፈልግ ትገልፃለች። ህብረተሰቡ ደግፎኛል፤ አግዞኛል እንዲሉ እንደምትፈልግም ትናገራለች።እነዚህ ልጆች ነገ ሲያድጉ የተለያየ የኃላፊነት ቦታ ላይ መቀመጣቸው አይቀሬ መሆኑንም ትጠቁማለች።

‹‹ትናንት ያልደገፋቸውንና ያላገዛቸውን ማህበረሰብ እንዴት አድርገው ያግዛሉ?›› ስትል የምትጠይቀው ዙበይዳ፤ ይሄ ችግር የግድ መቀረፍ እንዳለበትና ህብረተሰቡ በሰጣቸው ልክ እነርሱም መልሰው ስለሚሰጡ ዛሬ ላይ ለነዚህ ልጆች እየሰጠን ማሳየት አለብን ትላለች። ኢትዮጵያ ለእነዚህም ልጆች ሀገራቸው ስለሆነች ሌሎች ልጆቻችን ብቻ የሚረከቧት ሀገር አትኖርም ብለን ለራሳችን ዕውነቱን መንገር ይኖርብናል ስትል ትገልፃለች።

‹‹ልጆቻችን ሰላማዊና ጥሩ ኑሮ እንዲኖሩ ከፈለግን እኛ የእነሱን አቻ ጓደኞቻቸውን ማገዝ ነው ያለብንም›› ትላለች። ቂም ያልያዙና እኔን ትናንት የገፉኝ ማህበረሰብ ነው የማይሉ ሰላማዊ ልጆችን መፍጠር ከፈለግን የግድ እነሱም ሰላም መሆን አለባቸው ስትል ታስረዳለች። ‹‹በተደረገላቸው ልክ ሀገራቸውን ፣ወገናቸውን፣ሕዝባቸውን ማገልገል የሚፈልጉ፤ እነሱም ኃላፊነት የሚሰማቸው፤ እኔ ተደርጎልኛ እዚህ ደርሻለሁ፤ በመሆኑም የተቸገሩትን እረዳለሁ እንዲሉ ማድረግ ደግሞ የእኔ አላማ ነው ››ትላለች ዙቤይዳ።

ዙቤይዳ እንደምትለው እነዚህ የችግረኛ እናት ልጆች ትንሽ ሲደረግላቸው የሚረዱና ምንድነው የምታደርጉት ሲሏቸው እኔም የተቸገሩትን እረዳለሁ፤የራበውን አበላለሁ የሚሉ ናቸው። በመሆኑም ልጆቹ ያልሰጠናቸውን ስለማይሰጡን ዛሬ እየሰጠናቸው ማሳየት አለብን። ማህበረሰቡም የተቸገሩ ሰዎችን ሲያይ አንድ ብርና ሁለት ብር ከመስጠት ባሻገር ጎረቤቱ የሆኑትንና እሷ የምትደግፋቸውን ዓይነት እናቶችን መደገፍ አለበት። ‹‹ምንድነው ችግርሽ ፤ምንድነው ያጣሽው፤ እስቲ ምን ባደርግልሽ ነው የተሻለ የምትሆኚው›› በማለት ቀረብ ብለው ይህችን እናት ቢዋይዋት የተሻለ ትሆናለች።

እርሷ በማህበራዊ ሚዲያ ዛሬ እንዲህ ዓይነት ችግር ያለባት እናት አገኘሁ በምትልበት ሰዓት የማያውቋቸው ሰዎች ከአንድ ሺህ ብር ጀምሮ እስከ አስር ሺ ብር የሚልኩበት ሁኔታ መኖሩን ለማሳያ በመጥቀስ፤ እነዚህ ሰዎች የሚያውቋቸው ጎረቤቶች አጠገባቸው እንደነበሯቸው፤ ሆኖም እንዳላይዋቸው ታወሳለች። ‹‹እኔ ስናገር ግን እዛ ማዶ ላለውና ለማያውቁት ድጋፍ አደረጉ›› ስትልም በጎረቤትና በአካባቢያችን፤ በዘመዶቻችን፤ የሞተ ዘመድ ካለን ባለቤቱ እንዴት ነው ልጆቿን እያሳደገች ያለችው ብለን ልንጠይቅ ይገባል ስትል ትመክራለች።

ሕብረተሰቡ ስለ አኗኗራቸው ማወቅ እንዳለበትም ጠቁማ፤ በተለይ ፣ወላጆቻችን የጎረቤቶቻቸውን ኑሮ ስለሚያውቁ ‹‹እስኪ ይቺን ቅመሺ ብለው በርበሬ የሚልኩት ካላት ትቀምሳለች ከሌላት እንድትጠቀምበት ብለው እንደሆነም ታነሳለች። ይሄ ልጅ ሲያጠፋ ጎረቤት ያገባኛል ብሎ ለመቅጣት ብቻ ሳይሆን ሲራብም እናቱን በመደገፍ በኃላፊነት ጭምር ለመርዳት እንደሚበጅም ታነሳለች። አንድን ልጅ ጎረቤቱ ሁሉ ያሳድገዋል የሚባለው ለዚህ እንደሆነም ትጠቅሳለች። ይሄን አባባል በመረዳት ችግርን በጋራ መመከት እንዳለብን ታሳስባለች። ለኢትዮጵያዊያን ይሄ የኖርንበት ባህል በመሆኑ ሥራዬ ብለን ከያዝነው አይከብደንም ስትል ዙቤይዳ ትገልፃለች። ሰው ተቸገረ ሲባል ተረባርበን መደገፍ አለብንም ትላለች።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

በዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ አምድ ከበርካታ ዓመታት በፊት በጋዜጣው ለንባብ ከበቁ ዘገባዎ መካከል በብዛት ወንጀል ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩትን መራርጠናል:: ሌሎች ርዕሰ ጉዳዮችም ተካተዋል:: ከእነዚህም መካከል የሰማዕታት ሐውልት ስለ መመረቁ ፣ በወረባቡ አካባቢ ድርቅ በእጅጉ አስግቷል መባሉ፣ ሐሰተኛ ወሬን ሲያሰራጭ የነበረው ግለሰብ ተይዞ ለፍርድ ስለመቅረቡ፣ በሌላ በኩል ደግሞ 110 ታኒካ ማር በቤቱ ደብቆ ስለተገኘው ግለሰብም የወጣ መረጃን መለስ ብለን እናስታውሳለን:: በተጨማሪ ማህበረሰቡ በሳምንቱ ካጋጠማቸው ነገሮች መካከል ለአንባብያን ከሚያቋድሱበት "የሳምንቱ አጋጣሚ" ከተሰኘው ገጽ ላይ ሁለቱን በመቀንጨብ አቅርበናል::

### የሰማዕታት ሐውልት ተመረቀ

(ኢ.ዜ.አ)- ለሰላም ለዴሞክራሲና ለፍትህ መከበር ሲታገሉ በደርግ በግፍ ለተጨፈጨፉ ዜጎች መታሰቢያ ከሃምሳ ሺ አንድ መቶ ሰባ አምስት ብር በላይ ወጪ በጎንደር ከተማ የተሰራው ሐውልት ተመረቀ::

በደርግ አገዛዝ አስራ ሰባት አመታት የተከፈለውን መራራ ትግል የሚያንጸባርቁ ቅርጻ ቅርጾች የሰፈሩበት ይሄው ሐውልት በተመረቀበት ወቅት አቶ ታደሰ ካሳ የክልሉ ምክር ቤት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ባሰሙት ንግግር የጀግኖች ሰማዕታት በተገኘው የዲሞክራሲ መድረክ ላይ ቆመን መብታችንን በአግባቡ በመጠቀም ዘላቂ ጥቅማችንን ለማስከበር ስንችል ነው ሲሉ አስገንዘበዋል::

........................

በዚህም ሥነ ሥርዓት ላይ ከሃያ ሺህ በላይ ሕዝብ ተገኝተል::

(አዲስ ዘመን ታህሳስ 2 ቀን 1987 ዓ.ም)

### በወረባቡ ወረዳ ድርቅ አስግቷል

ደሴ፣ (ኢ.ዜ.አ)- በአምባሰል አውራጃ በወረባቡ ወረዳ በቆላው ክፍል አምሮና ገበሬዎችን አጓግቶ የነበረው የእህል አዝመራ በዝናብ እጥረት ምክንያት በእንጭጩ ጠውልጎ ከጥቅም ውጪ ወደመሆን ደረጃ መድረሱ ተገለጠ።

የወረዳው አስተዳደር ባለፈው ሳምንት ባስተላለፈልን ሪፖርት እንዳረጋገጡት በተለይ በቆላማው ክፍል በሚገኙት ሐደሬ፣ ኤጀርሳ፣ ጎደታና ዱበታ በተባሉት ቀበሌዎች የተዘሩት ማሽላ፣ ጤፍ፣ሰሊጥ፣ በቆሎ፣ ምስርና አተር በሚያሳዝን ሁኔታ ከመድረቃቸውም የተነሳ ገበሬዎቹ ከጥቅም ውጪ መሆናቸውን የለየላቸውን እየመረጡ ለከብቶች መኖ በማጨድ ላይ መሆናቸው ተረጋግጧል።

(አዲስ ዘመን ጥቅምት 5 ቀን 1968 ዓ.ም)

ተደብቆ የተገኘ 110 ታኒካ ማር ለመንግሥት ገቢ ሆነ

ጎባ፣(ኢ.ዜ.አ)- በጎባ ከተማ የኢኮኖሚ አሻጥረኞችን ለማጋለጥ እንዲቻል ፍተሻ በተደረገበት ወቅት ከአንድ ነጋዴ ቤት ተደብቆ የተገኘ 110 ታኒካ ማር ሰሞኑን በጨረታ ተሸ ገንዘቡ ለመንግሥት ገቢ ሆኗል።

..............

በሌላ በኩል ደግሞ በጊኒር ከተማ ሰሞኑን በተደረገው አሰሳ በ13 አሻጥረኛ ነጋዴዎች ሱቅና መኖሪያ ቤት ውስጥ ግምታቸው $2,291 የሆነ ልዩ ልዩ እቃዎች ተደብቀ ተይዘዋል።

ከእነዚህ አሻጥረኛ ነጋዴዎች ሱቅና መኖሪያ ቤት ተደብቆ የተገኘው በርበሬ፣ ክብሪት፣ ቅቤ፣ ጨው፣ ቀዝቃዛ መጠጥና ማር መሆኑን አንድ የማዘጋጃ ቤቱ ቃል አቀባይ ገልጧል። (አዲስ ዘመን ጥቅምት 9 ቀን 1969 ዓ.ም)

### የገበሬዎች ማኅበር የተደበቁ የጦር መሣሪያዎች አገኘ

ነቀምቴ፣(ኢ.ዜ.አ)- በቄለም አውራጃ የጋዋቄዶ ወረዳ ገበሬዎች ማኅበር ሰሞኑን ባደረገው አሰሳ አራት ጠመንጃና 21 ልዩ ልዩ አይነት ጥይቶች ከተደበቁበት ቦታ አግኝቷል። የተያዙት መሣሪያዎችና ጥይቶች በገበሬው ማኅበር ዕቃ ግምጃ ቤት ገቢ ሆነዋል።

(አዲስ ዘመን የካቲት 19 ቀን 1969 ዓ.ም)

### ቪዲዮ ቤቶች ተዘጉ

አሰላ(ኢ.ዜ.አ)- በአርሲ መስተዳድር ዞን በአሰላ ከተማ በሕገወጥ መንገድ በመኖሪያ ቤቶች በድብቅ የስርቆትና የብልግና ፊልሞች ያሳዩ ከነበሩ ቪዲዮ ቤቶች መካከል ዘጠና ስምንት በመቶ የሚሆኑት በቁጥጥር ስር መቃላቸውን የአሰላ ሲኒማ ቤት ገለጠ::

ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸው የተቋቋቋሙት እነዚህ የቪዲዮ ፊልም ቤቶች ለመንግሥት መክፈል የሚገባውን ቀረጥ ሳይከፍሉ ፊልሞችን በድብቅ በማስገባትና ወጣቶች ዘግናኝ የሆኑ ፊልሞችን እንዲመለከቱ በማድረግ ሥነልቦናቸውን ከመስረቅ ባሻገር ወርቃማ የትምህርት ጊዜያቶችን በመሻማት ጭምር ችግር ፈጥረው እንደነበር የሲኒማ ቤቱ ገልጦአል:: (አዲስ ዘመን ታህሳስ 10 ቀን 1972 ዓ.ም)

### የሐሰት ወሬ ያሰራጨው ተቀጣ

አዲስ ዓለም ,(ኢ.ዜ.አ)- የገጠር መሬት የሕዝብ እንዲሆን በወጣው አዋጅ ተደናግጦ የሐሰት ወሬ ሲያሰራጭ የተገኘው ደመቀ ለገሰ በስድስት ወር እስራት እንዲቃጣ ሰሞኑን ተወሰኖበታል:: (አዲስ ዘመን መስከረም 12 ቀን 1968 ዓ.ም)

### ተቆጣጣሪ በመምሰል ያጭበረበረው ተቀጣ

ደሴ፣ ኢዜአ በደሴ ከተማ ውስጥ ምንም አይነት ሥልጣን ሳይኖረው የአሥር አለቃ ነኝ በማለት ከገጠር ወደ ከተማ የሚገባውንና የሚወጣውን እህል፣ ስኳርና ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጦች በመፈተሽ ሲያወናብድ የተገኘው ዓሊ መሐመድ በ3 ወር እስራት እንዲቀጣ የ04-01-01 ቀበሌ ማኅበር የፍርድ ሸንጎ ከትናንት በስቲያ ወስኖበታል።

በተከሳሹ ላይ የእስራት ቅጣት ሊወሰንበት የቻለው ባልተሰጠው ሥልጣን በመንገድ ላይ እየጠበቀ ስኳርና ሸቀጥ ጭነው ወደ ገጠር የሚወጡትንና እህል ጭነው ወደ ከተማ የሚገቡትን መኪናዎች እያስቆመ በመፈተሽ የተመቸውን ጥቅም በመቀበል ሲለቅ ያልተመቸውን ደግሞ ወደ 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ በማቅረብ አወናብዶ ለማስቀጣት ሞክሮ እንደነበር በማረጋገጡ ነው:: (አዲስ ዘመን የካቲት 19 ቀን 1969 ዓ.ም)

### የሳምንቱ አጋጣሚ

እሁድ እለት አንባሳደር ቡና ቤት ቁጭ ብለን ሻይ ስንጠጣ አንድ የምናውቀው ሰው በመጠጥ ኃይል ተሸንፎ መዝጊያውን የከፈተ መስሎት ከመስተዋት ጋር ሲታገል በማየታችን በጣም አስቆናል::

**ሺመክት አለሙ**
**ከአዲስ ከተማ**

...............

አንድ መጽሔትና ጋዜጣ ሻጭ ልጅ ለአንድ የውጭ ዜጋ ታይም መጽሔት ለመሸጥ በሚያሳየው ጊዜ የውጭ ሰው ሐውማች ብሎ ሲጠይቀው ልጁ ጣቱን እያሳየ ዋን ብር ዋን ስሙኒ ብሎ መለሰለት:: (አዲስ ዘመን ታህሳስ 2 ቀን 1968 ዓ.ም)

# ዓለም አቀፍ

## በኬንያ አል-ሸባብ በተጠረጠረበት ጥቃት 5 ሰዎች በአደባባይ ተቀሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በኬንያ ጽንፈኛው እስላማዊ ቡድን አል-ሸባብ ሳይፈጽመው አልቀረም በተባለ ጥቃት አምስት ሰዎች አንገታቸው ተቀላ።

ይህ የሆነው በሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ በምትገኘው እና ለሶማሊያ ቅርብ በሆነችው የኬንያዋ ላሙ ግዛት ነው። አል-ሸባብ በተጠረጠረበት ድርጊት አምስት ሰዎች ከመገደላቸው በተጨማሪ በርካታ ቤቶች ተቃጥለዋል።

የፖሊስ ሰነድ ጥቃቱን ያደረሱት ግለሰቦች በቁጥር ከ20 እስከ 30 እንደሚሆኑ ያሳያል። ጥቃት አድራሾቹ ቅዳሜ ምሽት በሥፍራው የሚገኝ አንድ ገበያ ተቆጣጥረው አምስት ወንዶችን ከቤታቸው ጎትተው አምጥተው ቀልተዋቸዋል።

የዓይን እማኞች እንደገለጹት ጥቃቱን ያደረሱት ግለሰቦች የወታደር መለዮ ለብሰው ነበር። ከሁለት ሳምንታት በፊት የኬንያ መከላከያ ኃይል አባላትና ሌሎች ሰዎችን ያሳፈረ መኪና መንገድ ላይ የተቀበረ ተቀጣጣይ ፈንጅ ረግጦ በርካቶች ተጎድተው ነበር።

ባለፉት ወራት በኬንያ እና ሶማሊያ ድንበር ላይ የሚገኙ መንገዶች በመሰል ቦንቦች እየተሞላ መጥቷል። ቤት ውስጥ በሚሠራው ቦንብ [አይኢዲ] ምክንያት የፀጥታ አካላትን ጨምሮ በርካታ ሰዎች ከዚህ ቀደም ተገድለዋል።

ላሙ የተሰኘችው የባሕር ዳርቻ ኬንያና ሶማሊያ ከሚወሳኑበት ሥፍራ አቅራቢያ ትገኛለች። የአል-ሸባብ ታጣቂዎች በላሙ በተደጋጋሚ ጥቃት አድርሰዋል።

ከዘጠኝ ዓመታት በፊት የአል-ሸባብ ታጣቂዎች ፔኬቶኒ በተሰኘው ሥፍራ ቢያንስ 90 ሰዎችን መግደላቸው ይታወሳል። ኬንያ በላሙ በኩል ከሶማሊያ ጋር የሚያዋስናትን ድንበር ከዘጋች ከ10 ዓመት በላይ ሆኗታል። ነገር ግን ባለፈው ወር የሀገር ውስጥ ደኅንነት ሚኒስትሩ በላሙ፣ ጋሪሳ እና ማንዴራ በኩል ያሉ ድንበሮች በሚቀጥሉት 90 ቀናት እንደሚከፈቱ ገልጸዋል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።



## የተባበሩት መንግሥታት በርካቶች አደገኛ ዕፅ በመርፌ መውሰዳቸው አሳሳቢ ሆኗል አለ


**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የተባበሩት መንግሥታት ያወጣው ጥናት በርካቶች አደገኛ ዕፅ በመርፌ እየወሰዱ መሆኑን ማሳየቱን ይህም እንዳሳሰበው ገለጸ።

ዓለም አቀፍ የአደገኛ ዕፅ አጠቃቀምን እንዲጠቁም በሚል የተደረገው ጥናት ሕገ-ወጥ መድኃኒቶች መበርከታቸውን አሳይቷል። በፈረንጆቹ 2021 ለምሳሌ 13 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሰዎች አደገኛ ዕፅ በሲሪንጅ ወስደዋል።

ከዚህ ጥናት ቀደም ከነበረው ቁጥር 18 በመቶ ማሻቀብ ማሳየቱን የመንግሥታቱ የዕፅና ወንጀል ቢሮ ገልጧል። እንደ ፌንታኒል እና ሜታምፌታሚን ያሉ ዕፆች የሕገ-ወጥ መድኃኒት ገበያውን እንደተቆጣጠሩት የተባበሩት መንግሥታት ገልጿል።

በምድራችን የዕፅ ተጠቃሚዎች ቁጥር 23 በመቶ ሲጨምር ከዕፅ ጋር በተያያዘ የሚመጡ በሽታዎች ደግሞ 45 በመቶ አሻቅቧል አሊያም 40 ሚሊዮን ደርሷል።




ጥናቱ እንደሚጠቁመው ለአደገኛ ዕፆች ተጋላጭ የሆኑት የአእምሮ በሽታ ያለባቸው፤ ደከም ካለ ማሕበረሰብ የወጡና ወጣቶች ናቸው።

ምስራቅ አውሮፓ እና ሰሜን አሜሪካ በርካቶች በሲሪንጋ አደገኛ ዕፅ የሚወስዱበት ቦታ ሆኖ ተገኝቷል። ፌንታኒል የተሰኘው በክኒና መልክ የሚመጣ መድኃኒት ሰሜን አሜሪካን እያዳረሰ እንደሆነ ይህ ሪፖርት ጠቁሟል።

ከ18 ሀገራት በተወሰደ መረጃ መሠረት ወንዶች በአምስት እጥፍ ቀድመው አደገኛ ዕፅ መጠቀም ይጀምራሉ። ቀጥሎ ሴት ጓደኞቻቸውን ወደ ዕፅ መጠቀም ይጎትቷቸዋል። ዓለማችን በዕፅ ተጠቃሚ ብትሞላም ሕክምና ማግኘት የሚችለው ከአምስት ሰዎች አንዱ መሆኑን ድርጅቱ ገልጾ በተለይ ሴቶች የተለያየ ጋሬጣ እንደተደነቀረባቸው ያስነብባል።

የአደገኛ ዕፅ ተጠቃሚዎች ሕክምና የማያገኙበት ምክንያት ብዙና የተጠላለፈ ነው። አንደኛው ኮቪድ-19 ነው ተብሏል። ቀጥሎ ደግሞ ሕጋዊ ቅጣት ይደርስብኛል ብሎ መፍራት ነው። ማህበረሰባዊ ነቀፌታን መሸሽ፣ እንዲሁም ልጆችን ከማሳደግ ልከለከል እችላለሁ የሚል ፍራቻ ብዙዎች ሕክምና እንዳይሹ አድርጓቸዋል። የተባበሩት መንግሥታት ዕፅና ወንጀል ቢሮ አለቃ ጋዳ ዋሊ እንደሚሉት፤ በአብዛኛዎቹ ሀገራት ሰዎች ሕክምና ማግኘት ሲገባቸው ይህ ሳይሆን ቀርቷል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

"አደገኛ ዕፅ የሚያዘዋውሩ ቡድኖችን ማደን አለብን። እኒህ ቡድኖች ግጭትና ዓለም አቀፍ ቀውስ ሲኖር ይመቻቸዋል። በተለይ ደግሞ 'ሲንቴቲክ' ዕፆቻን በማምረትና በሕገ-ወጥ መንገድ በማዘዋወር ሰዎችን ክፉኛ እየጎዱ ነው" ብለዋል።

# ነፃ ሃሳብ

# ተማሪዎች ያለመጻሕፍት...

ከገጽ 5 የዞረ

የተዘጋጁ መጻሕፍት ህትመታቸው ተጠናቅቆ እስኪሰራጩም “ሶፍት ኮፒ”ያቸው ለትምህርት ቤቶችን እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡

### የታተሙ መጽሐፍትን የማድረስ ቃልና ትግበራው

የመማሪያ መጽሓፍት ለመማር ማስተማር ሂደት አይተኬ ሚና ያላቸው ቢሆንም፤ በ2015 የትምህርት ዘመን እነዚህ መጽሓፍት ከተማሪዎች ጋር ሳይተዋወቁ ዓመቱ መጠናቀቁ ይታወቃል፡፡ በዚህ ረገድ ዘግይቶም ቢሆን ለተማሪዎች እናደርሳለን ሲሉ የነበሩ የከተማ አስተዳደሮች እና ክልሎች ቢኖሩም፣ በቃላቸው መሰረት መገኘት ሳይችሉ ነው ተማሪና የመማሪያ መጽሓፍት እንደተነፋፈቁ የትምህርት ዘመኑ የተጠናቀቀው፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆኑ አንድ ሁለት መረጃዎችን ለመጥቀስ ልሞክር፡፡

መስከረም መጀመሪያ ላይ የመማር ማስተማር ስራውን አስጀመርኩ ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ስራ ከመጀመራቸው በፊት የቅድም ዝግጅት ስራዎች ስለማከናወኑ አሳውቆ ነበር።

ይሄ የቅድመ ዝግጅት ተግባር ደግሞ የትምህርት ቤቶች እድሳትን፣ የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የመጻሕፍትን ማስተዋወቅ እና የትምህርት ጉባዔ ማካሄድን ያካተተ ነው፡፡ ሆኖም የመጻሕፍት ዝግጅትና ስርጭትን አስመልክቶ የቢሮው ኃላፊ ህዳር 19 ቀን 2015 ዓ.ም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ በሰጡት ማብራሪያ፣ የመጻሕፍቶቹ ሶፍት ኮፒ ለየትምህርት ቤቶቹ ደርሶ የመማር ማስተማር ስራው እንዲጀመር ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝም ከተማ አስተዳደሩ መጻሕፍቱን በኮፒ ደረጃ በማዘጋጀት 1 ነጥብ 5 ሚሊየን የሚደርሱትን ለትምህርት ቤቶች አሰራጭቷል፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እስከ ህዳር 30 ድረስ የመጻሕፍቱ ህትመት ተጠናቅቆ 80 በመቶ የሚሆነው ስርጭት የሚከናወን ስለመሆኑ የቢሮው ኃላፊ መግለጻቸው ተነግሮ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ያለውን ሂደት ግን ከሚዲያዎችም፣ ከትምህርት ቢሮውም ይሄ ነው የሚል መረጃ ሊገኝ አልቻለም፡፡ ሆኖም እንደ ሌሎች ክልሎች ሁሉ በአዲስ አበባም ያሉ ትምህርት ቤቶች እና ተማሪዎች ከመማሪያ መጻሕፍት ጋር እንደተነፋፈቁ የትምህርት ዘመኑን ስለማጠናቃቸው ሌላ ነጋሪ ሳያሻን በየቤታችን ያሉ ተማሪዎችን ቦርሳ መመልከቱ በቂ ማስረጃ ይመስለኛል፡፡

እንደ አዲስ አበባው ሁሉ፣ በአፋር ክልልም ከ730 ሺህ በላይ የመማሪያ መጻሕፍት ህትመት እየተከናወነ ስለመሆኑ የካቲት 8 ቀን 2015 ዓ.ም አዲስ ዘመን ጋዜጣ ይዞት በወጣው ዘገባ አስነብቧል፡፡ ጋዜጣው የአፋር ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ አብዱ ሀሰንን ዋቢ አድርጎ እንዳስነበበው፤ በክልሉ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ለሚገኙ ከ186 ሺህ በላይ ተማሪዎች በየትምህርት ዓይነቱ በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ መሰረት የተዘጋጁ 730 ሺህ 633 መጻሕፍት ህትመት እየተከናወነ ነው፡፡

በዚሁ ጋዜጣ ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም በወጣ መረጃ ደግሞ፤ በክልሉ ለሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች 133 ሺህ በላይ መጻሕፍት ህትመት ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቆ መሰራጨታቸውን፤ እና ከ730 ሺህ በላይ መጻሕፍት ደግሞ በ150 ሚሊዮን ብር ወጪ ህትመታቸው እየተከናወነ መሆኑ ተዘግቧል፡፡

ከዚህ ዘገባ መረዳት የሚቻለው፣ ክልሉ በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት እንኳን ለሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች መጽሓፍትን በጊዜው ማድረስ ካለመቻሉም በላይ፤ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያሉት መጻሕፍት ህትመት ባለመከናወኑ ተማሪዎች መጽሓፍትን ሳያገኙ ዓመቱን ለማጠናቀቅ ተገድደዋል፡፡

11 ነጥብ 3 ሚሊዮን ተማሪዎችን ለመቀበል ተዘጋጅቻለሁ(ምንም እንኳና በኋላ ላይ በክልሉ ስምንት ሚሊዮን 28 ሺህ 958 ተማሪዎች መኖራቸውን ቢገለጽም)፣ መጻሕፍቶቹንም በሶፍት ኮፒ ለሁሉም ትምህርት ቤቶች አድርሻለው ያለው ኦሮሚያ ክልልም ቢሆን፤ የመጻሕፍት ህትመትና ሥርጭትን ጉዳይ በሁለተኛው መንፈቀ ዓመት እንደጀመረው መረዳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣ ጥር 13 ቀን 2015 ዓ.ም የወጣ መረጃ እንደሚያመለክተው፣ በክልሉ በትምህርት ገበታ ላይ ላሉ ተማሪዎች የአንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን መጻሕፍትን ብቻ ነው ህትመታቸውን ተጠናቅቆ ማሰራጨት የቻለው፡፡

ከዚህ ውጪ ያለው ተማሪ ገና ከመጻሕፍቱ ጋር ያልተዋወቀ ከመሆኑም በላይ፤ 35 ሚሊዮን የሚሆኑ የመማሪያ መጻሕፍት ገና በህትመት ሂደት ላይ ያሉ ናቸው፡፡ ችግሩ መጻሕፍቶቹ ህትመታቸው መዘግየቱ ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም እነዚህ መጻሕፍት ቢታተሙ እንኳን ሊያዳርሱ የሚችሉት የክልሉን ግማሽ ያህል ተማሪዎች ብቻ ነው፡፡

የዚህ ማረጋገጫ የሚሆነው ደግሞ በክልሉ ትምህርት ቢሮ በምክትል ቢሮ ኃላፊ ደረጃ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አማካሪ አቶ ኤፍሬም ተሰማ ተናገሩት የተባለው ሲሆን፤ ይሄም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የመማሪያ መጻሕፍትን ለሁሉም ተማሪዎች ተደራሽ ለማድረግ በአጠቃላይ 74 ሚሊዮን መጻሕፍት ያስፈልጋሉ ማለታቸው ነው፡፡

### የመጻሕፍቱ አለመድረስና ተጽዕኖው

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የመማሪያ ጻሕፍት ምን ያህል ዋጋ እንዳላቸው ለማወቅ የግድ በትምህርት ዓለም ውስጥ መኖርን አይጠይቅም፡፡ ምክንያቱም ይብዛም ይነስም ሁሉም በዚሁ መስመር አልፎ አይቶታልና። በመሆኑም በ2015 የትምህርት ዘመን በሥራ ላይ እንዲውል የተወሰነውን አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ተከትሎ የተዘጋጁ መጻሕፍት ለተማሪዎች አለመድረሳቸው ከፍ ያለ ተጽዕኖ መፍጠራቸው እሙን ነው፡፡ ይሄ ተጽዕኖ ደግሞ የትምህርት ጥራት ችግር አንድ ጉዳይ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡

ምናልባት ለመጻሕፍቱ በጊዜ አለመድረስ ትምህርት ሚኒስቴርም ሆነ ቢሮዎች የየራሳቸውን ምክንያት ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ በርግጥም በተለያዩ ጊዜያት እንደምንሰማው የመማሪያ መጻሕፍት ለተማሪዎች በወቅቱ ታትመው ለተማሪዎች ላለመድረሳቸው ቢሮዎቹ የየራሳቸውን ምክንያት ሲያቀርቡም ነበር፡፡ በዚህም ማተሚያ ቤቶች፣ በጀት፣ የውጭ ምንዛሬ እና የወረቀት ችግር፣ የታተሙ መጻሕፍትን ለማሰራጨት የሚወስደው ጊዜን የመሳሰሉት በ”እናቴ መቀነት አደናቀፈኝ”ነት ምክንያት ሲደረድሩ ተደምጠዋል፡፡

ይሁን እንጂ ይሄ የምክንያት ጋጋታ መጻሕፍት ለተማሪዎች በወቅቱ ተደራሽ ባለማድረጋቸው በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚፈጠረውን ከፍ ያለ ተጽዕኖ አያስቀረውም፡፡ ምክንያቱም፣ መጻሕፍቱ በወቅቱ ለተማሪዎች ባለመድረሳቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ እንዲሰሯቸው የሚሰጧቸውን መልመጃዎችን እንዳይሰሩ መሆናቸው፤ ከመጻሕፍቱ ተጨማሪ ሃሳቦችን አንብበው ለመረዳትና እውቀትን ለማንበር መቸገራቸው፤ መምህራንም ለተማሪዎች ማስታወሻን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ የትምህርት ጊዜያቸውን እንዲያባክኑ መገደዳቸው በግልጽ ታይቷል፡፡

የዘርፉ ምሑራን፣ መምህራን፣ ተማሪዎች እና ወላጆች ጭምር ይሄንኑ ሲናገሩ ቆይተዋል፡፡ ካለው ተጨባጭ ሁኔታም ሆነ ከወላጆች፣ ከተማሪዎችና ከመምህራን የዓመት ሙሉ ጥያቄና ቅሬታ መረዳት እንደሚቻለው፤ በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የተዘጋጁትን መጻሕፍት መምህራን እና ተማሪዎች ባለማግኘታቸው የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማሳለጥ ክፍተት መፍጠሩን ነው፡፡

ምክንያቱም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የቴክኖሎጂው መሰረተ ልማት ባልተስፋፋባቸው እና ትምህርት ቤቶቹም ከፍ ያለ የመሰረታዊ መሰረተ ልማት ፈተና ውስጥ ባሉ አገር ቀርቶ፤ የተሻለ አቅም አላቸው በሚባሉትም ቢሆን የመማር ማስተማር ሂደት ከመማሪያ መጻሕፍት ተፋትቶ የተከወነበት አጋጣሚ እምብዛም የሚታወስ አይደለም፡፡

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ፣ በአንድ በኩል የኢንተርኔትና ተያያዥ መሰረተ ልማቶች ያልደረሱባቸው አከባቢዎች የበዙ መሆናቸው፤ በሌላም በኩል ከህብረተሰቡ የኑሮ ደረጃ አኳያ የስማርት ስልኮችን፣ ታብሌቶችንና ላፕቶፖችን ከሚጠቀመው ማህበረሰብ አኳያ ሲታይ እነዚህን የመማሪያ መጻሕፍት በሶፍት ኮፒ ጥቅም ላይ ማዋልን አማራጭ አድርጎ ሙሉ የትምህርት ዘመን መጨረስ ጉዳቱን ያጎላዋል፡፡

ለዚህም ነው ወላጆች ለልጆቻቸው ሲጨነቁ፤ መምህራን በማስተማር ሂደቱ ሲባትሉ፤ ተማሪዎችም ከመጽሓፍ ውጪ በሆነው የመማር ማስተማር ሂደት ሲቸገሩ የተስተዋለው፡፡ ይህ ሁኔታም ለትምህርት ጥራት ከሚኖረው ጉዳት አንጻር የዘርፉ ምሑራንም ስለ አሉታዊ ተጽዕኖው ደጋግመው ሲገልጹ የተስተዋለው፡፡

ዘመኑ ከሚጠይቀው የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴ መምህር ተኮር ሳይሆን ተማሪ ተኮር ከመሆኑ አኳያም፤ የመማር ማስተማር ሂደቱ የተማሪዎች ቀድመው ማንበብና ራሳቸውን ለውይይት ማዘጋጀትን የግድ ይላል፡፡ ታዲያ ተማሪዎች መጻሕፍትን አግኝተው ይሄን ማድረግ ካልቻሉ፤ በመማር ማስተማር ሂደቱ የሚፈለገው የውይይትና የእውቀት ሽግግር እውን መሆን አይችልም፡፡

ይሄንን ተጽዕኖ አስመልክቶ ከሰሞኑ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ሃሳባቸውን የገለጹ ምሑራን እንዳሳሰቡትም፤ በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መሰረት የተዘጋጁ መጻሕፍትን በቶሎ ታትመው ለተማሪዎች በማድረስ በኩል ያሉ ክፍተቶች ቶሎ ካልተቀረፉ፤ አንድም ተማሪዎች በአግባቡ አንብበው ተገቢውን እውቀት እንዳይጨብጡ እንቅፋት ይፈጥራል፡፡ ሁለተኛም መምህራን ላይ ጫና በመፍጠር የትምህርት የጥራት መጓደልን ያስከትላል፡፡ ስለሆነም በተቻለ ፍጥነት መጻሕፍቱ ታትመው ለተማሪዎች እንዲደርሱ መሥራት ከሁሉም አካል የሚጠበቅ ትልቅና ቅድሚያ የሚሰጠው የቤት ሥራ መሆን አለበት የሚል ነበር፡፡

### በቀጣዩ የትምህርት ዓመት

ከመማሪያ መጻህፍት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ተማሪዎች እና መጻሕፍት ተራርቀው ያሳለፉበት 2015 የትምህርት ዘመን፤ ቀደም ብሎ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ካሳደረው ጫና እንዲሁም በትምህርት ጥራት ላይ ከሚፈጥረው ተጽዕኖ በተጓዳኝ፤ ከፍ ያለ ቅሬታን ይዞ አልፏል፡፡

ይሄ ጫና ሳይቃለል ቅሬታውም መልስ ሳያገኝ ደግሞ የ2016 ትምህርት ዘመን ደረስኩ ደረስኩ እያለ ነው፡፡ ዋናው ጥያቄ ታዲያ ቀጣዩ የትምህርት ዘመን (2016) እንደ አለፈው (2015) ሁሉ ተማሪና መጻሕፍት ተነፋፍቀው የሚያሳልፉበት ይሆናል? ወይስ ከተግባር የተፋታው የትምህርት ቢሮዎች ቃል ታድሶ መጻሕፍትና ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ለመገናኘት እድል ያገኛሉ? የሚለው ነው፡፡

በዚህ ረገድ ቢሮዎቹ የየራሳቸው ተግባራዊ ምላሽ ሊኖራቸው ቢችልም፤ ቀደም ሲል ከነበረው አፈጻጸማቸውና ብሂላቸው አኳያ ግን አሁንም የሚነሱ ስጋቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በኦሮሚያ ክልል በ2015 ቀድመው ታትመው ለተማሪዎች የተሰራጩ መጻሕፍት ክልላዊ ፈተና የሚወስዱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ ነበር፡፡ በሂደት እየታተሙ በስርጭት ላይ የነበሩት የአንደኛ፣ የሦስተኛ፣ የአምስተኛ እና የሰባተኛ ክፍል መጻሕፍት ናቸው፡፡

የሁለተኛ፣ የአራተኛ እና የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች የመማሪያ መጻሕፍትም እስከ መስከረም ወር ድረስ ሙሉ በሙሉ ታትመው ለ2016 የትምህርት ዓመት ለተማሪዎች እንዲደርሱ የሚደረጉ ናቸው፡፡ በጥቅሉ ሲታይ ግን በሕትመት ላይ የነበሩት 35 ሚሊዮን መጻሕፍትም ለ2015 ሊከናወኑ በእቅድ የተያዙ ናቸው፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ 2016 የትምህርት ዘመን ተማሪው መጻሕፍትን አግኝቶ ትምህርቱን ለመከታተል የሚችልበት እድል ስለመፈጠሩ እርግጠኛ መሆን ስለማይቻል፤ ከወዲሁ በምክንያት ከመታጠር ወጥቶ መጻሕፍትን አሳትሞ ለ2016 የትምህርት ዘመን ለተማሪዎች የማድረስ ጉዳይ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራበት ይገባል፡፡


በአፋር ክልልም ቢሆን፣ በሁለተኛው መንፈቀ ዓመት መጻሕፍት እንደደረሳቸው ከተነገረው የሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ውጪ፤ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ዛሬም ድረስ ከአዲሶቹ መጻሕፍት ሳይገናኙ የትምህርት ዘመኑን አጠናቅቀዋል፡፡ በሶፍት ኮፒ ማግኘት የቻሉትም ቢሆኑ፤ በክልሉ ካለው የኢንተርኔትና መሰረተ ልማትም ሆነ በሌሎች በበርካታ ምክንያቶች በሚፈለገው ልክ ላይጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

ከዚህ አኳያ የክልሉ ትምህርት ቢሮም ችግሩን የተገነዘበው ስለመሆኑ ቀደም ሲል የተጠቀሱት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም የክልሉ መንግሥት በ2015 የትምህርት ዘመን የታየውን የመማሪያ መጻሕፍት እጥረት በመፍታት በ2016 የትምህርት ዘመን ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚያስፈልገውን መጻሕፍት ለማዳረስ እየሰራ ስለመሆኑ ነው የተገለጸው፡፡

ሆኖም ይሄም እንደ 2015 የትምህርት ዘመን ሁሉ ከእቅድነት ያላለፈ ምኞት እንዳይሆን ከወዲሁ በልዩ ትኩረት መስራትና ቃልን በተግባር ማዋል፤ የቀደመውን አካሄድ መቀየር እና ተማሪዎችን ከመጻሕፍት ማገናኘት እጅጉን አስፈላጊ ነው፡፡ ይሄ ማሳሰቢያ፣ በማሳያነት ለተነሱት የኦሮሚያ እና አፋር ክልሎች ብቻ አይደለም። ይልቁንም ለሁለቱም ከተማ አስተዳደሮች እና ለሁሉም ክልሎች ትምህርት ቢሮዎች እንጂ፡፡

ምክንያቱም፣ በመጀመሪያ ሥራው ሁሉን አቀፍ ትኩረት የሚሻ ነው፡፡ ሲቀጥል በምክንያት ተከብቦ ውጤት መጠበቅ ስለማይቻል ነው፡፡ እንዴት ካሉም፣ ምክንያት በመደርደር በተማሪዎች፣ በመምህራንና ወላጆች ላይ የሚፈጥረውን ጫና መቀነስ አይቻልም፤ ምክንያት በመደርደር የመጻሕፍት በወቅቱ ያለመድረስ በትምህርት ጥራት ላይ የሚፈጥረውን አሉታዊ ተጽዕኖ አያስቀርም፤ ምክንያት መደርደር የተሟላ የኢንተርኔት መሰረተ ልማት የማያገኙ እና በኑሮ ደረጃ ምክንያት ላፕቶፕ፣ ታብሌት እና ስማርት ስልክ ማግኘት የማይችሉ ተማሪዎች ከመጻሕፍቱ ሳይተዋወቁ አንድ ዓመት ያሳለፉበትን ሂደት አይቀይርም። በመሆኑም ቃልን በተግባር ለማዋል ምክንያት ሳይሆን ትጋት እጅጉን አስፈላጊ መሆኑን ተረድቶ፤ ይታተማሉ ወይም እየታተሙ ነው የሚባሉ መጻሕፍት በወቅቱ ትምህርት ቤቶች እንዲደርሱ ማድረግ፤ ትምህርት ቤቶችም ያለመሳቀቅ መጻሕፍቱን ለተማሪዎቻቸው እንዲያድሉ፤ ተማሪዎችና መምህራኑም በመጻሕፍቱ አለመኖር ምክንያት ከሚደርስባቸው ጫና እንዲላቀቁ፤ ወላጆችም ከሚፈጠርባቸው ጭንቀት እንዲድኑ፤ ከዚህም በላይ እንዲያንሰራራ የሚፈለገው የትምህርት ጥራት ከምኞት ያለፈ እውነት እንዲሆን ማድረግ የቀጣዩ የትምህርት ዘመን ተማሪዎች ያለ መጻሕፍት የማይማሩበት ዓመት በማድረግ ውስጥ የሚገለጽ ውጤት ተደርጎ ሊወሰድ የተገባ ነው፡፡

# ስፖርት



## ዶፒንግ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ስጋት በመሆኑ ባለድርሻ አካላት ሊረባረቡ ይገባል

ዓስማየሁ ግዛው

ኢትዮጵያ በዓለም ታላላቅ የስፖርት ውድድር መድረኮች ውጤታማ ሆና ሰንደቅ ዓላማዋ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ያደረገው አትሌቲክስ ነው። ይህ ስፖርት በዓለም አትሌቶች አበረታች ቅመሞችና መድኃኒቶች (በዶፒንግ) ተጠቃሚነት ምክንያት አደጋ ውስጥ መግባቱ ይታወቃል። ይህ አደጋ ካንዣበባቸው ሀገራት አንዷ ኢትዮጵያ ነች። ኢትዮጵያ ይህን በስፖርቱ ላይ የተቃጣ አደጋ ለመታገል ባለፉት ዓመታት አበረታች ሥራዎችን መስራቷ የሚታወቅ ሲሆን አሁንም ከአደጋው ስጋት ነፃ አልወጣችም።

የዶፒንግ ጉዳይ ለኢትዮጵያ አሁንም አሳሳቢ መሆኑን ተከትሎ ችግሩ ከፍተኛ ደረጃ በመድረሱ ባለድርሻ አካላት ርብርብ ሊያደርጉ እንደሚገባ ተጠቁሟል። ከችግሩ ስፋትና ክብደት አንጻር ከባለድርሻ አካላት ጋር አፋጣኝ ውይይትና ለችግሩ መፍትሔ መፈለግ ብቸኛ መንገድ መሆኑም ገልጿል። የጉዳዩን አሳሳቢነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በአበረታች ቅመሞችና መድኃኒቶች ቁጥጥርና መከላከል ላይ ያተኮረ “ችግሩን እንዴት እንዋጋ” የሚል የምክክር መድረክ ሰኔ 17 2015 ዓ.ም ከባለድርሻ አካላት ጋር ተከናውኗል።

ሁሉም ባለድርሻ አካላት በተገኙበት የምክክር መድረክ በአትሌቲክስ ፌዴሬሽንና በኢትዮጵያ ፀረ አበረታች ቅመሞችና መድኃኒቶች ቁጥጥር ባለስልጣን አማካኝነት የአበረታች ቅመሞችና መድኃኒቶችን ስጋት የሚዳስሱ የመነሻ ጽሑፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ በቀረቡት የመነሻ ጽሑፎችም አበረታች ቅመሞችና መድኃኒቶች (ዶፒንግ) አትሌቲክስ ከሁሉም ስፖርቶች በበለጠ ቀዳሚው ተጋላጭ እንደሆነ ተመላክቷል፡፡ የመነሻ ጽሑፎቹ ቀርበው ውይይት ከተደረገባቸው በኋላም የመፍትሄ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡




በስፖርቱ የተከለከሉ ወደ 10 የሚደርሱ ቅመሞችና መድኃኒቶች ጥቅም ላይ እየዋሉ እንደሚገኙ ተጠቁሟል፤

በስፖርቱ የተከለከሉ ወደ 10 የሚደርሱ ቅመሞችና መድኃኒቶች ጥቅም ላይ እየዋሉ እንደሚገኙ ለውይይት በቀረቡት ፅሁፎች የተጠቆመ ሲሆን፣ ”ይሄንን ሸንጎ የጠራነው ጎረቤታችን ኬንያ ለቅሶ ላይ ስለሆነች ነው” ሲሉ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከፍተኛ የህክምና ባለሙያ ዶክተር አያሌው ጥላሁን ለውይይት ባቀረቡት ጽሑፍ ወቅት ተናግረዋል።

ዶክተር አያሌው በአትሌቲክስ የማይነጥፍ ውጤት እየተመዘገበ ቢሆንም የአበረታች ቅመሞችና መድኃኒቶች ከፍተኛ ስጋት በመሆናቸው አደጋውን ለመቀልበስ የባለድርሻ አካላትን ሰፊ ርብርብ እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል። መድኃኒቶቹን በመሸጥና አትሌቶች እንዲጠቀሙ በማድረግ ከስፖርተኞችና ማናጀሮች በተጨማሪ የሙያ ሥነ-ምግባራቸውን የማያከብሩ የህክምና ባለሙያዎች እንዲሁም የህክምና ተቋማት ትልቁን ድርሻ መያዛቸው ችግሩ ውስብስብና አስቸጋሪ እንዳደረገውም ዶክተር አያሌው አስረድተዋል።

ከኢትዮጵያውን ማናጀሮች ባሻገር የውጭ ሀገር ዜጎች በነጻነትና መድኃኒቶችን እያዘዋወሩ አትሌቶችን በማታለል እንዲጠቀሙ በማድረግ ግንባር ቀደም ተዋናዮች በመሆናቸው የባለድርሻ አካላት በዚህ ላይ ቁጥጥር በማድረግ ርብርብ ሊያደርጉ እንደሚገባም ተጠቁሟል።

ተጨማሪ የመነሻ ጽሑፍ ያቀረቡት የኢትዮጵያ ጸረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ዳይሬክተር አቶ መኮንን ይደርሳል፣ አበረታች ቅመም (ዶፒንግ) “በዜጎቻችን ላይ የስነልቦና ችግርን እያስከተ ነው” በማለት አስረድተዋል፡፡ ባለስልጣኑ የአበረታች ቅመሞች ምርመራና ቁጥጥር በዓለም አቀፍ በጣም እየተጠናከረ በመምጣቱ በቁጥጥሩ ላይ ሰፊ ሥራዎችን እየሰራ እንደሆነም አስታውሰዋል፡፡ የዓለም አቀፉ ፀረ አበረታች መድኃኒቶች ቁጥጥር ባለስልጣን ኢትዮጵያ ቁጥጥሯን ማጠናከር እንደሚኖርባት ማሳሰቢያ መስጠቱንም ተናግረዋል፡፡ አትሌቶች እየተቀጡ ብዙ ርቀት መሄድ ስለማይቻልም የምርመራ ስራው ሊቀጥልና ባለድርሻ አካላት ሊተባበሩ እንደሚገባ ማሳሰቡን ተናግረዋል፡፡ በዚህም መሰረት ባለስልጣኑ 34 የሚሆኑ መድረኮችን በማዘጋጀት አጫጭር እና የገጽ ለገጽ ሥልጠናዎችን በመስጠት 3425 የሚሆኑ ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ በሚሊዮን ለሚቆጠር ማህበረሰብ ግንዛቤ መፍጠር እንደተቻለ ጠቁመዋል፡፡

ባለሥልጣኑ በበጀት ዓመቱ 657 ለሚሆኑ ስፖርተኞች ምርመራ ያደረገ ሲሆን የተጋላጭነት ዳሰሳ ጥናትም ሰርቷል። የዳሰሳ ጥናቱ የአትሌቲክስ ስፖርት የመጀመሪያው የዶፒንግ ተጋላጭ እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡ በተደረገው ምርመራም 7 የሕግ ጥሰት የፈጸሙና አበረታች ቅመሞች ተጠቅመው የተገኙ አትሌቶች እንዳሉ ታውቋል፡፡ ምርመራው ተጠናቆ ሕጋዊ ሂደቱን ከጨረሰ በኋላ የአትሌቶቹ ዝርዝር ይፋ እንደሚደረግም ተገልጿል፡፡ የሕግ ጥሰት ከፈጸሙት አትሌቶች ውስጥ ሰባ በመቶ የሚሆኑት ቻይና ላይ በተደረጉ ውድድሮች የተያዙ መሆናቸውም ተጠቁሟል፡፡ አበረታች ቅመሞችን ተጠቅመው የተገኙ ስፖርተኞች ከአስተዳደራዊ እርምጃ በተጨማሪ በወንጀል ሊጠየቁ እንደሚችሉም ታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጸረ አበረታች ቅመሞችና መድኃኒቶች ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር በመሆን ያደረገው የጸረ ዶፒንግ የምክክር መድረክ ባለ 7 ነጥብ የአቋም መግለጫ በመስጠት ተጠናቋል፡፡ በዚህም መሰረት ባለድርሻ አካላት በጋራ በመሆን በርብርብ መስራት፤ በሕገ ወጥ የዶፒንግ መድኃኒቶችና ንጥረ ነገሮችን የሚሸጡና አትሌቶችን እንዲጠቀሙ የሚያደርጉ ሕገ ወጦችን በጋራ መቃወም፣ ለሕግም እንዲቀርቡ ማድረግ፣ አትሌቶችን በሕጋዊ መንገድ ከኢትዮጵያ በመውሰድና በልዩ ልዩ የዓለም መድረኮች በውድድር እንዲሳተፉ በማድረግ የኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሚያደርጉ የአትሌት ተወካዮችን ማበረታታትና ከዚህ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ሀገርን የሚጎዳ ተግባር የሚፈጽሙ ተወካዮችን ማጋለጥ፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የአትሌቲክስ ልማቱን በተሻለ አሰራርና ዕቅድ እንዲፈጽም፣ የኢትዮጵያ ጸረ አበረታች ቅመሞችና መድኃኒቶች ባለስልጣን ምርመራውንና የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራውን በአግባቡ እንዲሰራ ጫና በማድረግ የድርሻቸውን እንደሚወጡ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡